ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቅጽ02 ቁ14
መጋቢት 2018 ዓ.ም



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

## እንደራሴ

እንደራሴ በብርጅሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

## መልክዓ - ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው :: ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሠተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው ::

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ::
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

BRIDGE Research & Innovation - Parliaments. Peace. Policy

+251 99 808 5013
+251 115 57 74 96
info@bridge-et.org
https://bridge-et.org/
UNECA, SA Building, 9th Floor,
Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.

## ማውጫ


በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች ....................................................................3
1. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት ........................................................................5
1.1 የጸደቁ ሕግጋት....................................................................................5
1.2 ረቂቅ ሕግጋት ..................................................................................... 6
1.3 አስረጂ መድረኮች ..................................................................................... 8
2. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ........................................................................ 11
2.1 የተቋማት ሪፖርቶች ........................................................................ 11
2.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች..................................................................18
2.2.1 የመስክ ጉብኝቶች .................................................................................. 18
3. የውክልና ሥራዎች ..........................................................................................21
3.1 የቤንሻንጉል/ጉሙዝ መራጮች ምን ጉዳዮችን አነሱ? ...........................................21
3.2 ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ...........................................................................21
3.3 የኦሮሚያ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች......................................................... 22
3.4 ከሱማሌስ? .................................................................................................... 24
3.5 ድሬዳዋ ምን አነሳች? ...................................................................................... 24
3.6 ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የተሰሙት............................................................. 24
4. የፓርላማው ዲፕሎማሲ .............................................................................................25
5. እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው .......................................................................30
5.1 ዓለም ዓቀፉን የሴቶች ቀን ..........................................................................30
5.2 የምርምር ሥራ ምክክር መድረክ ......................................................................30
5.3 የውክልና ሥራ ላይ የተካሄደ ውይይት .........................................................31
5.4 የሥልጠና መድረክ..........................................................................................31
6. እንደራሴዎቹ እና ምርጫ 2018 .....................................................................................33
7. ኢትዮጵያ ምን ተስማማች? ............................................................................................ 34
8. የብሪፎ ዳሰሳዊ ምልከታ፦አዲሱ የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ለውጦች እና ሙግቶች ......36

**የማሻሻያው ዳራ** ........................................................ 36

**አሟጓቹ አንቀጽ** ........................................................ 36

**አዲሱ ሕግ ምን ይዟል?** ........................................................ 37

ሀ፦ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ መዋሃድ፤ ........................................................ 37

ለ፦ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ እና የሕግ የበላይነት፤ ........................................................ 38

ሐ፦ የዲጂታል ማስረጃዎች ዕውቅና፤ ........................................................ 38

መ፦ የዐቃቤ ሕግ ሥልጣን እና ክስ መመስረት፤ ........................................................ 38

ሠ፦የምሥክሮች እና የጠቋሚዎች ጥበቃ፤ ........................................................ 39

ረ፦ የፍርድ ቤት ሥነ-ሥርዓት ቅልጥፍና፤ ........................................................ 39

ሰ፦ ባህላዊ ሥርዓታት እና የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ፤ ........................................................ 39

**ሦሥት ነጥቦችን በወፍ በረር...** ........................................................ 39

ሀ፦ ዋስትና ........................................................ 39

ለ፦ የጥፋተኝነት ድርድር ........................................................ 40

ሐ፦ የማስረጃ ሕግ ........................................................ 41

**እንደ መውጪያ** ........................................................ 42

9. **የብሪፎ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ የኢትዮጵያ ሴቶች የእንደራሴነት መንገድ፤ ከማርች ስምንት ማዶ** ........................................................ 44

የሴቶቻችን ትናንቶች ........................................................ 44

እንዴት ይሳተፉ? ........................................................ 46

የሴት እንደራሴዎቹ የውክልና ምጣኔ በወፍ በረር ........................................................ 49

የሴቶች ውክልና በእንደራሴዎች ምክር ቤት ........................................................ 51

የሴቶቹ ተሳትፎ በቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ ........................................................ 51

የሴቶች ውክልና በፌዴሬሽን ምክር ቤት ........................................................ 53

የብሪፎ ምክረ-ሐሳቦች ........................................................ 54

## ኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ መጋቢት ክራሞት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ መጋቢት የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን አከናውኗል። ከእነዚኽ ዋንኛ ኃላፊነቶቹ መካከልም፣ ሕግጋትን ማጽደቅ፣ የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማት ሪፖርቶችን ማድመጥ፣ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎችን መከወን እና የመስክ ጉብኝቶችን ማድረግ የወሩ የምክር ቤቱ አበይት ክንውኖች ነበሩ። ከዚያ ባለፈ ከሐምሌ እስከ መስከረም መጨረሻ ድረስ ከሚያካሂዱት የውክልና ሥራ በተጨማሪ፣ ከየካቲት የለጠቀውን የውክልና ሥራቸውን አከናውነዋል። ከዚኽ አኳያም፣ በዚኹ ወርኃ መጋቢት በዛ ያሉ እንደራሴዎቻቸውን ወደ ተመረጡባቸው የምርጫ ክልሎች በመላክ፣ ዜጎች ያሳስቡናል ባሏቸው ጉዳዮች ዙሪያ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮችን አካሂደዋል። ይኽች የእንደራሴ ዐሥራ ዐራተኛ ዕትምም፣ እነኽን ጉዳዮች በመልክ በመልካቸው አጠናቅራ እና ለወሩም እንዲሆን ኹለት የብሪፎ ዳሰሳዊ ምልከታዎችን አካታ እንዲኽ ተጠናቅራለች።

## በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች

| 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን | ቀን | አጀንዳዎች |
|---|---|---|
| **12ኛ መደበኛ ስብሰባ** | መጋቢት 15 | * በኢፌድሪ እና በኮርያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ለህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ፕሮጀክት ምዕራፍ 2 ማስፈጸሚያ የሚውል እና ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን ተጨማሪ የብድር ስምምነቶችን ማጽደቅ፤ |
| | | * በኢፌድሪ እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ለታዳሽ፣ የተቀናጀ፣ ዘላቂ ኃይል እና ዲጂታላይዜሽን ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ማጽደቅ፤ |
| | | * በኢፌድሪ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔት እና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን ሦሥተኛ ተጨማሪ የብድር ስምምነት ማጽደቅ እና፣ |
| | | * የጉምሩክ ዐዋጅን እንደገና ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ ዐዋጅን መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መምራት፤ |

| | | |
|---|---|---|
| **13ኛ መደበኛ ስብሰባ** | መጋቢት 24 | * የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ረቂቅ ሕግን መርምሮ ማጽደቅ፤ |
| **14ኛ መደበኛ ስብሰባ** | መጋቢት 29 | * የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና አሥተዳደር ረቂቅ ዐዋጅን መርምሮ ማጽደቅ፤ |
| | | * የመረጃ ነጻነት እና የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ረቂቅ ዐዋጆችን መርምሮ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መምራት፤ |

# 1. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ መጋቢት **ኹለት ሕግጋትን** ሲያጸድቁ፣ **ሦሥት ረቂቆችን** ይመለከታቸዋል ወዳላቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ለዝርዝር ዕይታ ሲልኩ፤ **በሦሥት ረቂቅ ዐዋጆች** ዙሪያ ደግሞ የአስረጂ መድረኮችን አካሂደዋል።

## 1.1 የጸደቁ ሕግጋት

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ መጋቢት ኹለት ሕግጋትን አጽድቋል። በምክር ቤቱ 13ኛ መደበኛ ስብሰባ የጸደቀው ቀዳሚው ዐዋጅ፣ **የኢፌድሪ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ረቂቅ ዐዋጅ** ሲሆን፣ የረቂቅ ዐዋጁን የውሳኔ ሐሳብ እና ሪፖርት ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግስቱ እንደነበሩ ተጠቅሷል።

ሰብሳቢዋም፣ ረቂቅ ሕጉ በወንጀል ፍትሕ አሥተዳደር ሥርዓት የወንጀል ፍርድ ሂደት የተጠርጣሪን እና የተከሳሽን እንዲኹም በወንጀል ምክንያት የተጎዱ ሰዎችን ሰብዓዊ መብቶች ለማክበር እና ለማስከበር የሕግ የበላይነት በማስፈን የአሰራር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።

ከዚኽ ባለፈም፣ የተቀላጠፈ የፍትሕ ሥርዓት እንዲኖር ለማስቻል እና ልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴን እንዲኹም ለተጎጂዎች ካሣ የሚከፈልበትን አግባብ ያካተተ ዓለም ዓቀፍ መርህን የተከተለ ረቂቅ ሕግ እንደሆነ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት አያይዘው አስረድተዋል። እንደራሴዎቹ በበኩላቸው ረቂቅ ዐዋጁ የዘገየ ቢሆንም፣ በሕዝቡ ዘንድ የቅሬታ ምንጭ የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ወቅቱን የሚመጥን ዐዋጅ በመሆኑ የፍትሕ ሥርዓቱን በማዘመን ወቅቱን የመጠነ አግልግሎት ለመስጠት ረቂቅ ዐዋጁ ሚናው የጎላ መሆኑን ጠቅሰዋል።

አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ በተራቸው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ዘመኑን የዋጀ፣ ጊዜ ወስዶ የተሰራበት፣ ለሌሎች ሕግጋት ጭምር ትምህርት የሚወሰድበት እና አስተማሪ የሆነ እንዲኹም የምክር ቤቱን አሰራር በግልጽ ያሳየ መሆኑን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። በመጨረሻም እንደራሴዎቹ ረቂቅ ዐዋጁ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1410/2018 ሲሉ በኹለት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አጽድቀውታል። (ይኽንን ዐዋጅ አስመልክቶ የብሪጅን አጠር ያለ ዳሰሳ በገጽ 36 ይመለከቷል)።



*እንደራሴዎቹ በከፊል፣ ዐዋጁ በጸደቀበት ዕለት፤*

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች በዚኹ ወር በነበራቸው 14ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቁት ኹለተኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት**

**እና አሥተዳደር ረቂቅ ዐዋጅ** ሲሆን፤ በምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት የተዘጋጀውን የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት ሰብሳቢው የተከበሩ ሰለሞን ላሌ እንደነበሩ ተጠቅሷል።

ረቂቅ ዐዋጁ በመንግስት ብቻ የሚሰጠው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በቂ ባለመሆኑ ወቅቱ የሚጠይቀውን የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሥርዓት እንዲዘረጋ ምቹ መደላድል እንደሚፈጥር የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ በዲጂታል ግብርና ኤክስቴንሽን የሚያማክሩ እና የመረጃ ቅብብሎሽ አገልግሎት የሚሰጡ የግል ባለሀብቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የሆኑ ድርጅቶች እየታዩ በመሆኑ በግብርና ኤክስቴንሽን ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ረቂቅ ዐዋጅ መሆኑን አስገንዝበዋል ተብሏል።

ከዚያ ባለፈም፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ ጥራት እና ፍትሐዊነት ቁጥጥር ትኩረት የሚሻ በመሆኑ አገልግሎት የሚሰጠው በተመዘገበ እና የብቃት ማረጋገጫ ባገኘ አገልግሎት አቅራቢ መሆን እንደሚኖርበት ዐዋጁ የአሰራር ሥርዓት እንዳስቀመጠ ያነሱት የተከበሩ ሰለሞን፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ፣ በዘርፉ ምርትን በብዛት፣ በጥራት እና በቀጣይነት ለማሳደግ የግብርና ኤክስቴንሽን ከፍተኛ ሚና እንዳለው ገልጸዋል ተብሏል።

የተወሰኑ እንደራሴዎች በበኩላቸው፣ ከግብርና ምርምር የሚገኙ እና ከውጭ የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን የግብርና ባለሙያው ለአርሶ አደሮች በተግባር ማሳ ላይ በማሳየት አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው አስተያየት መስጠታቸውን ዘገባው ጠቅሷል። በመጨረሻም እንደራሴዎቹ በረቂቅ ዐዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረጉ በኋላ፣ ረቂቅ ዐዋጁን ዐዋጅ ቁጥር 1411/2018 ሲሉ በሙሉ ድምጽ አጽድቀውታል።



*የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፣ የረቂቁን የውሳኔ ሐሳብ ሲያቀርቡ፤*

## 1.2 ረቂቅ ሕግጋት

የኢፌድሪ እንደራሴዎች፣ በወሩ ይመለከታቸዋል ወዳሏቸው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በዝርዝር ይታዩ ዘንድ የላኳቸው፣ ሦሥት ረቂቅ ዐዋጆችን እንደነበረ ተመላክቷል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ መጋቢት 15 ቀን በዋለው 12ኛ መደበኛ ስብሰባው **የጉምሩክ ዐዋጅን እንደገና ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ዐዋጅ** ላይ በሰፊው ተወያይቷል። የዐዋጁን መሻሻል አስፈላጊነት አስመልክቶ የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ አጭር ማብራሪያ አቅርበው፣ ምክር ቤቱም ቢሻሻሉ እና ቢካተቱ ባላቸው ዐበይት ጉዳዮች ላይ ከተወያየ በኋላ ረቂቅ ዐዋጁን ዐዋጅ ቁጥር 9/2018 በማድረግ ለዝርዝር እይታ ለኘላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቶታል።

እንደራሴዎቹ በወሩ የደረሳቸው ኹለተኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡትን የዳኝነት አገልግሎት ለማዘመን እና ተቋማዊ አሠራራቸውን ለመቀየር የተዘጋጀው አዲስ ረቂቅ ዐዋጅ** ነበር። ምክር ቤቱ በወሩ በነበረው 14ኛ መደበኛ ስብሰባ ይኽንን ረቂቅ ዐዋጅን የመራው፣ በምክር ቤቱ ለሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፤ አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎም፣ ይኽ አዲስ ረቂቅ ዐዋጅ ለረጅም ዓመታት ሲሠራበት የቆየውን እና አኹን ካለው ነባራዊ ኹኔታ እና ከፍትሕ ሥርዓት ለውጥ ጋር የማይጣጣመውን የቆየ ዐዋጅ ሙሉ በሙሉ የሚተካ መሆኑን ገልጸዋል።

አፈ-ጉባኤው አክለውም፣ ረቂቁ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የመልካም አሥተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እና ተያያዥ ማነቆዎችን በዘላቂነት ለመፍታት ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን አብራርተዋል ተብሏል። ረቂቅ ዐዋጁ የዳኞች አሥተዳደር ጉባኤ አደረጃጀት እና የዳኞች ምልመላ ሥርዓት ግልጽ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ፣ የፍትሕ ሥርዓቱን ተዓማኒነት ለማሳደግ ትኩረት እንደሰጠም ተጠቅሷል። ረቂቅ ዐዋጁም፣ በቀጣይነት በሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት የሕግ ባለሙያዎች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ሰፊ መድረክ እንደሚፈጠር ተጠቁሟል።



*አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ በረቂቁ ዐዋጅ ውይይት ወቅት፤*

እንደራሴዎቹ፣ በዚኹ 14ኛ መደበኛ ስብሰባቸው የተመለከቱት ሌላይኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የቀረበላቸውን ረቂቅ ዐዋጅ** ሲሆን፣ ዐዋጁንም ለዝርዝር እይታ በምክር ቤቱ ለዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርተውታል። የረቂቅ ዐዋጁን አስፈላጊነት አስመልክተው የተናገሩት አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ቀደም ሲል በነበረው ዐዋጅ የመረጃ ነጻነትን እና መገናኛ ብዙኃንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በአንድ ዐዋጅ መውጣታቸው የመረጃ ነጻነት ሕግ በተገቢ ሁኔታ፣ በተሟላ የአሥተዳደር ሥርዓት እና በአፈጻጸም ግልጽነት እንዳይቀርብ በማድረጉ እና ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር በማጣጣም የመረጃ ነጻነት ዐዋጅ ራሱን አስችሎ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ የቀረበ መሆኑን ገልጸዋል።

አፈ-ጉባኤው አክለውም፣ ማንኛውም ሰው በመንግሥት አካል እጅ የሚገኝ መረጃ የመጠየቅ፣ የማግኘት እና የማሰራጨት ነጻነት ይበልጥ በማረጋገጥ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሕገ-መንግሥቱ እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን የመረጃ ነጻነት ይበልጥ እውን ለማድረግ

ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ የቀረበ መሆኑንም አብራርተዋል ተብሏል።



*እንደራሴዎቹ፣ የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የቀረበላቸውን ረቂቅ ዐዋጅ ሲያደምጡ፤*

## 1.3 አስረጂ መድረኮች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ መጋቢት ካካሄዳቸው የአስረጂ መድረኮች መካከል ቀዳሚው፣ **በአቬዬሽን ሴኪዩሪቲ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ** ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ይመለከታቸዋል ከተባሉት ጋር የተወያየበት መድረክ ነበር።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ዘርፉ ቁልፍ የሆነ የአገራችን ደኅንነት መገለጫ በመሆኑ ቋሚ ኮሚቴው ትኩረት ሰጥቶ በኢትዮጵያ አቬዬሽን ሴኪዩሪቲ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተጨማሪ የውይይት መድረክ በማዘጋጀቱ ተጨማሪ ግብዓት መገኘቱን ገልጸው፣ ኹሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል።

ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ በበኩላቸው፣ ረቂቅ ዐዋጁ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ ዘርፉን በአፍሪካ ብሎም በዓለም ይበልጥ ከፍ የሚያደርግ እንዲኹም የአቬዬሽን ደኅንነትን የበለጠ የሚያጠናክር መሆኑን አስገንዝበዋል።

በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የረቂቅ ሕግ ጥናት ጉዳዮች መሪ ሥራ አሥፈፃሚ ወ/ሮ ታደለች አማረ ደግሞ፣ በረቂቅ ሕጉ የማሻሻያ አንቀፆች ዙሪያ የጋራ አረዳድ እንዲኖር እና ተጨማሪ ግብዓቶችን ለማካተት ከዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች እና ከተለያዩ አገራት ልምዶች አንፃር ማብራሪያ አቅርበው ውይይት መካሄዱን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል።

በውይይቱም ከባለድርሻ አካላት ግልጽነት ያስፈልጋቸዋል የተባሉ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች ተነስተው፣ ከብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት፣ ከኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት፣ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እንዲኹም ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት በመጡ የሥራ ኃላፊዎች ምላሽ እና ማብራሪያ እንደተሰጠባቸው ተዘግቧል።



*በአቬዬሽን ሴኪዩሪቲ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ የተካሄደው የአስረጂዎች መድረክ በከፊል፤*

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች በወርኃ መጋቢት ያካሄዱት ኹለተኛው የአስረጂ መድረክ፣ **በጉምሩክ ዐዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ ሲሆን፤ መድረኩን የመራውም በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄም፣ አገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ ባለፉት ጊዜያት በርካታ የተሻሻሉ ዐዋጆች መኖራቸውን ገልፀው፣ የጉምሩክ ዐዋጅ መሻሻሉ የገቢ እና ወጪ ንግዱን ከማሳለጥ ባሻገር የኮንትሮባንድ ንግድን በመከላከል ረገድ የጎላ ፋይዳ እንደሚኖረው አመላክተዋል።

ሰብሳቢው አክለውም፣ የማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ ለአሠራር እንቅፋት የሆኑ የዐዋጁን አንቀፆች ለይቶ አስቸኳይ እልባት መስጠትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ጠቁመው፣ ተቋሙ ከኮንትሮባንድ ነጋዴዎች አቅም ጋር የሚመጣጠን ተቋማዊ አቅም ለመገንባት ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋልም ተብሏል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነሩ ደበሌ ቃበታ፣ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ለምታደርገው ጥረት እንቅፋት የሚሆኑ አሠራሮችን ለማሻሻል፣ እንዲኹም እንደ አገር ከተደረገው የገንዘብ ማሻሻያ እና ከዓለም ዓቀፋዊ እና አሕጉራዊ ድንጋጌዎች ጋር የተናበበ ለማድረግ በማስፈለጉ የተደረገ ማሻሻያ እንደሆነ ገልፀዋል።

ኮሚሽነሩ አያይዘውም ረቂቅ ዐዋጁ ኮንትሮባንድ የጫኑ ተሽከርካሪዎችን መውረስን በተመለከተም፣ ከዚኽ በፊት በነበሩ ዐዋጆች ይታይ የነበረውን የመልካም አሥተዳደር፣ የፍትሕ፣ የአሠራር፣ የአወሳሰን እንዲኹም ከባለተሽከርካሪዎች መብት ጋር የተገናኙ መብቶችን በአግባቡ ያለማክበር ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚያግዝ መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

ረቂቅ ዐዋጁ በኮንትሮባንድ ከተወረሱ ንብረቶች ሽያጭ የሚገኘው ገቢ የተቋሙን አሠራር ለማዘመን፣ እንዲኹም የኮንትሮባንድ ንግድን በመከላከል ረገድ ተሳታፊ ለሆኑ ባለድርሻ አካላት አቅም ግንባታ ሥራ የሚውልበትን አሠራር ያካተተ መሆኑን የተናገሩት ደግሞ፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነሩ አዝዘው ጫኔ ናቸው ተብሏል።



*በጉምሩክ ዐዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ የነበረው የአስረጂ መድረክ፤*

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **በኅብረት ሥራ ማኅበራት ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ ያዘጋጀው የሕዝብ እና የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክም፣ የወሩ ሌላይኛው የአስረጂ መድረክ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰለሞን ላሌም፣ በውይይቱ መክፈቻ ላይ እንደገለፁት የኅብረት ሥራ ማኅበራት በአገር ኢኮኖሚ ልማት ላይ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ገልፀው፣ የኢንዱስትሪ እና የግብርና ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለአባላቱ በማቅረብ፣ የብድር አቅርቦት

በማመቻቸት፤ እንዲኹም የዜጎችን የቤት ችግር በመፍታት የፋይናንስ ተጠቃሚነትን እውን በማድረግ በኩል ጉልህ አስተዋጽዖ እያበረከቱ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።

ሰብሳቢው አያይዘውም፣ ከኢኮኖሚ ማሻሻያው በፊት 125,453 የኅብረት ሥራ ማኅበራት የነበሩ ቢሆንም፣ አብዛኞቹ ተልዕኳቸውን በተገቢው ለማሳካት የአደረጃጀት፣ የሰው ኃይል እና የግብዓት ችግር የነበረባቸው መሆኑን ጠቅሰዋል።



*የአስረጂ መድረኩ በከፊል፤*

## 2. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው መጋቢት ወር፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች **የዐሥር የፌደራል ተቋማትን** የበጀት ዓመቱን ከመንፈቅ የሥራ አፈጻጸም እና የኦዲት ግኝት ክንውን፣ የየተቋማቱን የሥራ ኃላፊዎች ወደ አዳራሻቸው ጠርተው አድምጠዋል፤ ያሳሰቧቸውን አስተያየቶች እና ጥያቄዎችን አንስተውም፣ የኃላፊዎቹን ማብራሪያዎች ሰምተዋል።

### 2.1 የተቋማት ሪፖርቶች


የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወሩ የተቋማት ሪፖርት ግምገማ የጀመረው፣ **የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴርን እና የተጠሪ ተቋማቱን** የ2018 በጀት ዓመት የ6 ወራት የሥራ ክንውን በመገምገም ነበር። የተቋሙን የመንፈቅ ሪፖርት ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትሯ የተከበሩ ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል የተቋሟቸውን ሪፖርት ለቋሚ ኮሚቴው አቅርበዋል።

ሚኒስትሯም በሪፖርታቸው፣ የአሠሪ እና የሠራተኛ ጉዳይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ የመጣ እንደሆነ አስረድተው፣ በሥርዓት እንዲመራ እና ዜጎች ክብራቸው ተጠብቆ እንዲሰሩ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የዲጂታላይዝድ ሥራ መጀመራቸውንም አስገንዝበዋል።

ሚኒስትሯ አክለውም የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር የሥራ ዕድል ፈጠራ ከ2017 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የአገር ውስጥ የሥራ ዕድል ፈጠራ በ24.9 በመቶ ዕድገት ሲያሳይ፤ የውጭ አገር የሥራ ዕድል ፈጠራ ደግሞ የ52 በመቶ ብልጫ ማሳየቱን አስረድተዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እና ተጠሪ ተቋማቱ በ6 ወራት በኹሉም ዘርፍ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሻለ ለውጥ እያሳየ መምጣቱን ገልጸዋል።

ሰብሳቢው አክለውም የኢንዱስትሪ ሰላም እና ደኅንነት፣ የሥራ ባህል እና ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እና የተጠሪ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ከክልሎች ጋር በመቀናጀት በዕቅድ በመሥራት የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸው ለሌሎች ተቋማት ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው ብለዋል ተብሏል።

በሌላ በኩል ሰብሳቢው፣ የሥራ ማዕከላትን ተደራሽ በማድረግ በሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ የሆኑ አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ማሳደግ እና የፈጠራ ሐሳብ ያላቸውን ወጣቶችን አወዳድሮ በመሸለም በዕቅድ ልክ አለመፈጸሙን ተናግረው፣ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች እና ቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት የተመረቁ ወጣቶች የሥልጠና አቅምን በማሳደግ ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚገባ ማስገንዘባቸው ተጠቅሷል።



*የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትሯ የተከበሩ ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል የተቋሟቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤*

ይኸው ቋሚ ኮሚቴ በዚኹ መጋቢት ወር ያደመጠው የ2018 በጀት ዓመት የመንፈቅ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት **የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**ን ሪፖርት ሲሆን፤ ቋሚ ኮሚቴውም ዩኒቨርሲቲው ውጤታማ የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መግለጹ ተዘግቧል። ከአዲስ አበባ ከተማ አሥተዳደር ጋር በመተባበር ብዙ ሥራዎችን እየሰራ እንደሆነ እና በተለይም የአዲስ አበባ ወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶችን በማጥናት እና በማማከር እየሰራ ያለው ሥራ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነትን እየተወጣ እንደሆነ የሚያሳይ መሆኑን የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ ገልፀዋል ተብሏል።

ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማር በተጨማሪ ብዙ በጆርናል የታተሙ ጥናት እና ምርምሮችን መሥራቱ በአፍሪካ ተወዳዳሪ ተቋም መሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑ ባለፈ፣ ግማሽ የሚሆኑት የጥናት እና የምርምር ሥራዎች ከዓለም ዓቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር የተሰሩ መሆናቸው የተቋሙን ዓለም ዓቀፋዊ የዲፕሎማሲ ከፍታ እንደሚያስረዳ ሰብሳቢው አያይዘው ጠቁመዋል። ሰብሳቢው አክለውም፣ ተቋሙ የኹሉም ኢትዮጵያዊ ኃብት እና ኩራት በመሆኑ ከኹሉም የኢትዮጵያን አካባቢ ተማሪዎችን መቀበል የሚያስችል አካታች እና ፍትሐዊ መስፈርት መጠቀም እንዳለበት አመላክተዋል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ.ር. ሳሙኤል ክፍሌ በበኩላቸው፣ በመንግሥትም ይሁን በራሳቸው ከፍለው የሚማሩ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ከተቀረፁት 66 ፕሮግራሞች ውስጥ ከ20 በማይበልጡት ላይ ብቻ መማር እንደሚፈልጉ መናገራቸው ተጠቅሷል።



*የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ.ር. ሳሙኤል ክፍሌ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በዚኹ መጋቢት ወር ወደ አዳራሹ ጠርቶ ሪፖርታቸውን ካደመጠላቸው ፌደራላዊ ተቋማት መካከል፣ **የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር** ይገኝበታል። ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቴዎስም፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸውን እና የተጠሪ ተቋማቱን የበጀት ዓመት የመንፈቁን ሪፖርት፣ በምክር ቤቱ ለውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርበዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ደማ ነጎ፣ ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ተጠቃሚነቷን ለማሳደግ ከአገራት ጋር የተፈራረመቻቸው ስምምነቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ተግባር እንዲቀየሩ በትኩረት መሥራት ይጠበቃል ሲሉ ማሳሰባቸው ተሰምቷል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በበጀት ዓመቱ የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በቱሪዝም፣ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት እና

ኢኮኖሚ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመዘገብ መሥራቱን ቋሚ ኮሚቴው በተለያዩ ስልቶች ማረጋገጡን ጨምረው የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ ኢትዮጵያ የዓለምን ትኩረት በመሳብ ዓለም ዓቀፍ እና አህጉር ዓቀፍ ጉባኤዎችን በውጤታማነት ማከናወን በመቻሏ ሂደት ውስጥ የአገርን ገፅታ በመለወጥ ረገድ ስኬታማ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል ተብሏል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቴዎስ በበኩላቸው፣ በበጀት ዓመቱ ከቡድን 20፣ ከብሪክስ ፕላስ እና ከሌሎች ዓለም ዓቀፍ እና አህጉር አቀፍ ተቋማት ፊት የተሰሚነትን ደረጃ የሚጨምሩ ቁልፍ ተግባራት መከናወናቸውን አብራርተዋል።

በመሆኑም የተለያዩ ዘርፎች የኢትዮጵያን ፍላጎት እና ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቁ እና ለዕድገት መሰረት የሆኑ ስምምነቶች የተፈጸሙ መሆናቸውን ሚኒስትሩ መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። በዚህም ሂደትም ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ያስጠበቀ ገለልተኛ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በመተግበር ጠቃሚ ጉዞ እያደረገች መሆኑን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አክለው ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ የባሕር በር ጉዳይ ወደ ተጨባጭ ውጤት የመቀየር ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ሲሉ መናገራቸው የተዘገበው ደግሞ፣ ምክትል ሰብሳቢው ዶ.ር. የተከበሩ ፈትሂ ማህዲ መሆናቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያሳያል።



*ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቴዎስ፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፤*

በዚኹ ኹለተኛ ቅጽ ዐሥራ ዐራተኛ የእንደራሴ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ መጋቢት፣ የበጀት ዓመት የመንፈቁን የሥራ አፈጻጸሙን ያቀረበው ሌላይኛው ተቋም፣ **የሰላም ሚኒስቴር** ሲሆን፣ ሪፖርቱን ያደመጠው ደግሞ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር።

የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትሩ የተከበሩ መሀመድ እድሪስ፣ የሰላም አደረጃጀቶችን በየደረጃው በማቋቋም እና በማጠናከር፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለሰላም ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እያደረጉ እንደሚገኙ በሪፖርታቸው ላይ አንስተዋል።

ሚኒስትሩ አያይዘውም፣ ከሌሎች የፌደራል ተቋማት እና ክልሎች ጋር ቅንጅታዊ አሠራሮችን በማጠናከር፣ ተፈናቃዮችን ወደቀያቸው እንዲመለሱ በማድረግ፣ እንዲኹም በኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀጣይ ለሚካሄደው 7ኛው አገራዊ ምርጫ በሰላም እንዲጠናቀቅ ለማድረግ የጋራ ውይይትና ሥምምነት መደረጉን አብራርተዋል። ከተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት

ከቀረቡ 33 ቅሬታዎች መካከል ባለፉት ሥድስት ወራት ሃያ አምስቱን መፍታት መቻሉንም ሚኒስትሩ አክለው ገልጸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ የበጎ ፈቃድ ሥራ ትውልድን በመገንባት ረገድ ፋይዳው የጎላ በመሆኑ ተቋማዊ በማድረግ እና የሕግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ወጣቶች በአካባቢያቸው ብሎም በሌሎች አካባቢዎች የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ከማድረግ አንፃር በትኩረት መሥራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል።

ሰብሳቢው አክለውም፣ በሠላም እጦት የመጀመሪያ ተጠቂዎች ሴቶች እንደመሆናቸው መጠን ሴቶችን ከማብቃት እና ወደ ኃላፊነት ከማምጣት አንፃር ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ማሳሰባቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል።

ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ በበኩላቸው፣ ከኦዲት ነቀፌታ የፀዳ የፋይናንስ አሠራርን ከመከተል እና ተፈናቃዮችን ወደነባር ቀያቸው እንዲመለሱ ከማድረግ አንፃር የተከናወኑት ተግባራት አበረታች መሆናቸውን ጠቁመው፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል ተብሏል።



*የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትሩ መሀመድ እድሪስ፣ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

የወሩ ሌላይኛው ተረኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው **የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር** ሲሆን፣ ሪፖርቱን ያደመጠውም በምክር ቤት የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ታውቋል። የተቋሙን የ2018 በጀት ዓመት የስምንት ወራት የሥራ ክንውን ሪፖርት ያደመጡት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ አሻ ያህያ፣ የንግድን ሥርዓቱን ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ እና ተደራሽ ለማድረግ የተሰሩት የኦንላይን ፈቃድ አሰጣጥ፣ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት የሚያስፈልገውን ረጅም ሂደት አሰራር በመዘርጋት መሻሻሉ ትልቅ እምርታ የታየበት በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት መናገራቸው ተሰምቷል።

ሰብሳቢዋ አክለውም፣ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት እና አምራች እና ሸማቹን በቀጥታ ለማገናኘት የእሁድ እና ቅዳሜ ገበያ ማዕከላትን በማስፋት የተወሰዱት እርምጃዎች የሚበረታቱ ተግባራት መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ይኽም ገበያን ለማረጋጋት ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል ተብሏል። የተከበሩ ወ/ሮ አሻ፣ ከነዳጅ ጋር በተያያዘ በወቅቱ ያለው ዓለም ዓቀፍ

ቀውስ እንዳለ ሆኖ፣ ነዳጅን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ብዙ መልስ የሚያስፈልጋቸው ቦታዎች በመኖራቸው ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባም አሳስበዋል።

የንግድ ዘርፍ ማኅበራት ሚናቸው የጎላ በመሆኑ የንግዱን ዘርፍ ከማሳደግ እንዲኹም ሕገ-ወጥነትን ከመከላከል አንፃር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቅርብ ክትትል ማድረግ እንዳለበት የተናገሩት ደግሞ፣ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዮሐንስ መስፍን መሆናቸው ተጠቅሷል።

የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ.ር. ካሳሁን ጎፌ በበኩላቸው፣ የነዳጅን ተደራሽነት ለማስፋፋት በዘርፉ ያለውን ከፍተኛ ሕገ-ወጥ ተግባር በመቆጣጠር ከፍተኛ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ከቋሚ ኮሚቴው ጋር በትብብር እንደሚሰሩ ተናግረዋል። ሚኒስትሩ አክለውም፣ በቋሚ ኮሚቴው በጥንካሬ የተነሱትን ለማስቀጠል እንዲኹም ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለማሻሻል እንደሚሰሩ ገልጸዋል ተብሏል።



*የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ.ር. ካሳሁን ጎፌ፣ በሪፖርታቸው ወቅት፤*

በዚኹ ወርኃ መጋቢት፣ ከላይ እንደተጠቀሱት ሌሎች የፌደራል ተቋማት ኹሉ፣ የዚኽን በጀት ዓመት የመንፈቅ የሥራ አፈጻጸሙን ያቀረበው፣ **የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ** ሲሆን፤ ሪፖርቱንም ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና በሰጡት አስተያየት፣ ከውጭ አገር የሚገባውን ስኳር ለማስቀረት እና የአገር ውስጥ ፍጆታን ለመሸፈን የስኳር ፋብሪካዎች በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ሰብሳቢው አክለውም የአገር ውስጥ የስኳር ፍጆታን መሸፈን ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያ ስኳርን ወደ ውጭ በመላክ የዓለም ገበያን ሰብራ እንድትገባ የስኳር ፋብሪካዎቹ አቅደው ሊሠሩ እንደሚገባ አሳስበዋል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ በበኩላቸው፣ የስኳር ምርትን በማሳደግ በስንዴ ምርት የመጣውን እምርታ መድገም እንደሚቻል ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ዋና ሥራ አሥፈጻሚው አቶ ወዩ ሮባ በሰጡት ማብራሪያም፣ የስኳር ፋብሪካዎች ስኳር ለማምረት የሚፈጅባቸውን ጊዜ በማሳጠር ስኳርን በአጭር ጊዜ ለማምረት ጥረት እያደረጉ ቢሆንም፣ በተለይ አዳዲስ የስኳር ፋብሪካዎች ሲገነቡ ያላካተቷቸው ነገሮች ስላሉ ለማሟላት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አብራርተዋል ተብሏል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ወጪ፣ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል የተከናወነው

**የጉምሩክ ኮሚሽን** የሥራ አፈጻጸም ኦዲት ሪፖርት ግምገማም፣ የወሩ አንዱ የተቋማት የሥራ አፈጻጸም ክንውን ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. የሺመቤት ደምሴ፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እና ከወቅታዊ የንግድ ሥርዓት ጋር የተጣጣመ የታሪፍ አወቃቀር እንዲኖር የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማዘመን እንደሚገባ ገልጸዋል።

ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ ዕቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ የሚደረገው ቁጥጥር ክፍተት የታየበት መሆኑንም የጠቀሱት ሰብሳቢዋ፣ የመንግስት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ማረጋገጥ እና የቀረጥ ነጻ መብቱ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑም ክትትል ሊደረግበት እንደሚገባም አሳስበዋል ተብሏል። የኦዲት ወሰኑ ከ2014 እስከ 2017 ዓም. የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሚሸፍን እንደሆነ የተናገሩት የፌዴራል ዋና ኦዲተሯ ወ/ሮ መሠረት ዳምጤ በበኩላቸው፣ የጉምሩክ ሥራ በባህሪው ተለዋዋጭ በመሆኑ የዘመነ ቴክኖሎጂ እስከ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንዲኹም ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ግንዛቤ በመያዝ የተቀመጡትን የሕግ ማዕቀፎች በአግባቡ መተግበር እንደሚገባ ምክረ-ሐሳብ ሰጥተዋል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነሩ ደበሌ ቃበታ በበኩላቸው፣ በቀረቡት የኦዲት ግኝቶች ላይ የታየ ክፍተቶችን ለመሙላት እና የዲጂታል አሰራርን በማጠናከር ቁጥጥሩን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ይሰራል ብለዋል ተብሏል።



*የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕን ሪፖርት ሲያደመጡ፤*

ይኸው የመንግስት ወጪ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የገመገመው ሌላው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት፤ **የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽንን** የሥራ አፈፃፀምን ሲሆን፤ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. የሸመቤት ደምሴ፣ የፌደሬሽኑ የትጥቅ ስርጭት አሰራር የተመዘገበ እና አግባብነት ያለው የስርጭት መስፈርት ሊኖረው እንደሚገባ ገልጸዋል ተብሏል። ሰብሳቢዋ አክለውም፣ በአትሌቲክሱ ዘርፍ የእድሜ ተገቢነትን ለማረጋገጥ የተጀመረው አዲስ አሰራር መልካም መሆኑን ጠቅሰው፣ ይኽንን እና ሌሎች ተጨማሪ የመለያ ዘዴዎችን በመጠቀም ይበልጥ ማጠናከር እንደሚገባ አቅጣጫ ማስቀመጣቸው ተዘግቧል።

የፌደራል ዋና ኦዲተሯ መሰረት ዳምጤ በበኩላቸው፣ ቀደም ሲል የነበሩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ፌደሬሽኑ እየሰራ ያለው ሥራ የሚደነቅ መሆኑን ጠቅሰዋል። ይኹን እንጂ ከስፖርት ትጥቅ እና ከሥልጠና ቁሳቁስ አያያዝ እንዲኹም ከሽልማት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ያሉ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ግልፅ የሆነ የማስፈፀሚያ ሰነድ እና አሰራር እንደሚያስፈልግም

ጨምረው ገልጸዋል ተብሏል። የፌደሬሽኑ ሥራ አሥኪያጅ ኮማንደር አትሌት ስለሺ ስህን በበኩላቸው፣ ያሉትን ክፍተቶች በመቅረፍ አሰራሩን በቀጣይ በመመሪያ ለማስደገፍ እና ወደ ሕጋዊ ማዕቀፍ ለማስገባት በቀጣይ እንደሚሰሩ መናገራቸው ተዘግቧል።



*የፌደሬሽኑ ሥራ አሥኪያጅ አትሌት ስለሺ ስህን በኦዲት ክዋኔ ሪፖርቱ ወቅት፤*

እንጋፋው **የብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት**ም፣ በዚኹ ወር ሪፖርታቸውን ካቀረቡት ተቋማት መካከል አንዱ ሲሆን፤ የተቋሙን ሪፖርት ያደመጠውም፣ በምክር ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ ድርጅቱ ሕትመቶችን በብቃት እና በጥራት በማተም ለመረጃ ስርጭት፣ ለትምህርት መስፋፋት፣ ሚስጢራዊ ሕትመቶችን በማተም ለፋይናንስ እና ለሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ደኅንነት እና ለሥራ መቀላጠፍ ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚያበረከት አንስተዋል።

ሰብሳቢው አክለውም፣ ድርጅቱ ባቀደው ልክ ሥራዎችን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር ተያይዞ ጤናማ የሀብት አሥተዳደር እና የፋይናንስ ሥርዓትን በመተግበር የኦዲት ግኝቶች ላይ የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎችን በሚመለከት ጠንካራ ክትትል ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ስለሺ ኮሬ የሕትመት ዘርፉን በዘመናዊ አሰራር ማነቃቃት እንደሚያስፈልግ ገልጸው፣ የመጽሐፍ ሕትመትን በሚመለከት የትምህርት ስብራት ችግርን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ታቅዶ ሊስራ ይገባል ማለታቸው ተጠቅሷል።

የብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ዋና ሥራ አሥፈፃሚው ሽታሁን ዋለ በበኩላቸው፣ ከመጽሐፍ ሕትመት ጋር ተያይዞ በውጭ አገር የሚታተሙ ሕትመቶች እንዲቀሩ እና በአገር ውስጥ እንዲታተሙ አቅም መፍጠር የሚያስችሉ ጥናቶችን አድርገው እየተሰራ እንደሆነ መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*የብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ዋና ሥራ አሥፈፃሚው ሽታሁን ዋለ፣ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

የአንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በጊዜ ምጣኔ በመጨረሻ የገመገመው፣ **የኢትዮጵያ ፐልፕ እና ወረቀት አክስዮን ማኅበር** የ2018 በጀት ዓመት የሥድስት ወራት አቅድን አፈጻጸምን ሲሆን፤ የተቋሙን ሪፖርት ያደመጠውም በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ እንደነበር ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ የኢትዮጵያ ፐልፕ እና ወረቀት አክሲዮን ማኅበር ከ55 ዓመታት በላይ ለኢትዮጵያ ዕድገት፣ ለለውጥ እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ ተናግረዋል።

አክሲዮን ማኅበሩ በተያዘው በጀት ዓመት በዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎችን በብቃት መፈፀሙን፣ጤናማ የሀብት አሥተዳደር እና የፋይናንስ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረጉን ትኩረት የሚደረግባቸው ግምገማዎች እንደሆኑ ሰብሳቢው ገልጸዋል ተብሏል። የኢትዮጵያ ፐልፕ እና ወረቀት አክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አሥኪያጅ ባይሳ ተመስገን በበኩላቸው፣ አክሲዮኑ ወረቀት እና ካርቶን እንደሚያመርት አስረድተው፣ የወረቀት ምርት ዕቅድ አፈፃፀም በመጀመሪያው ሥድስት ወራት 52.7 በመቶ እንደሆነ እና ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ደግሞ በ29.3 በመቶ ዝቅ ማለቱን ተናግረዋል።

የወረቀት ምርት አፈፃፀሙ ከዕቅድ በታች የሆነው በማሽን መቆም ችግር እንደሆነ የጠቀሱት ሥራ አሥኪያጁ፣ የጥገና እና ቴክኒክ ማኔጅመንቱን በማስተባበር እንደገና ወደ ሥራው እንዲመለስ መደረጉን ለቋሚ ኮሚቴው አስረድተዋል ተብሏል።



*የመንግስት ልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የኢትዮጵያ ፐልፕ እና ወረቀት አክስዮን ማኅበርን የመንፈቅ ሪፖርት ሲያደምጡ፤*

## 2.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የኢፌድሪ አንደራሴዎች፣ በወሩ ውስጥ ምንም ዓይነት የተቋማት ጉብኝቶችን ባያደርጉም ቅሉ፣ የተወሰኑ የመስክ ምልከታዎችን ማካሄዳቸውን እንደራሴ ያሰባሰበቻቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፤ ብዙዉን የመስክ ጉብኝታቸውም በ'የክልሎቹ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችን መሆኑም ተመልክቷል።

### 2.2.1 የመስክ ጉብኝቶች

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች፣ በዚኽ ወር ካደረጓቸው የመስክ ጉብኝቶች አብዛኛውን ድርሻ የያዘው፣ በ'የክልሎቹ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ያደርጓቸው የመስክ ጉብኝቶች ናቸው። በወሩ ቀዳሚ ተጎብኚ የነበረው ማሳያ ዩኒቨርሲቲም፣ **ደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ** ሲሆን፣ ዩኒቨርሲቲውን የጎበኘው ደግሞ በምክር ቤቱ የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማር ሥራው በተጓዳኝ በግብርናው እና በሌሎች ዘርፎች የአካባቢውን ኅብረተሰብ ችግር ሊፈቱ የሚችሉ በርካታ የምርምር እና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል። ሰብሳቢው አክለውም፣ ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው ኅብረተሰብ የወተት፣ የአትክልት እና የፍራፍሬ እንዲኹም ሌሎች የግብርና ምርቶችን ወደ ገበያ በማስገባት ገበያ ለማረጋጋት ያደረጋቸው ጥረቶች በምሳሌነት የሚወሰዱ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ትምህርት ክፍል መምህር እና ተመራማሪ የሆኑት ረዳት ፕሮፌሰር ሶሬሳ ሹማ በበኩላቸው፣ ዩኒቨርሲቲው የአርሶ አደሩን ችግሮች ለመፍታት የሚረዱ የተለያዩ ምርምሮችን እያከናወነ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አብራርተዋል ተብሏል።



*ቋሚ ኮሚቴው ደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲን በጎበኙበት ወቅት፤*

በዚኹ ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት የተጎበኘው ሌላው የወሩ ማሳያ ተጎብኚ ዩኒቨርሲቲ **ወለጋ ዩኒቨርሲቲ** ሲሆን፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮም፣ የወለጋ አካባቢ በግብርና፣ በእንስሳት፣ በማዕድን ዘርፍ የሚታወቅ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ወደ አፕላይድ ሳይንስ በሚያደርገው ሽግግር የአካባቢውን ፀጋ እና የማኅበረሰቡን ተጠቃሚነት ታሳቢ ያደረገ ሊሆን እንደሚገባ ማስገንዘባቸው ተጠቅሷል።

በዩነቨርሲቲው ውስጥ የሚገኘው የማስተማሪያ ሆስፒታሉም፣ ለአጎራባች ክልሎች አገልግሎት እየሰጠ ያለ እና ከፍተኛ ጫናዎች ያሉበት በመሆኑ በቀጣይ ሆስፒታሉ የተሻሉ የማስፋፊያ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ማጠናከር እንደሚገባው ሰብሳቢው አሳስበዋል ተብሏል። የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቱ ዶ.ር. ተስፋዬ ለማ በበኩላቸው፣ ዩኒቨርሲቲው ሰላም እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲጎለብት ከአካባቢው ኅብረተሰብ ጋር በመቀናጀት ሰፊ ሥራዎች መሰራታቸውን እና ለውጥ መገኘቱንም ጠቁመው፣ ይኽንንም አጠናክሮ ለማስቀጥል እየተሰራ መሆኑን መናገራቸው ተዘግቧል።



*የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝታቸው ወቅት፤*

በተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ የተመራው ይኸው ቋሚ ኮሚቴ፣ የመስክ ጉብኝት ያካሄደበት ሌላይኛው ዩኒቨርሲቲ፣ **አርባምንጭ ዩኒቨርስቲ** ሲሆን፤ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ ዩኒቨርሲቲው በአገራችን

ከሚገኙ የመጀመሪያው ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ መሆኑን ጠቁመው፣ ዩኒቨርሲቲው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቀጥሎ ወደ ፊት ራስ ገዝ ይሆናሉ ተብለው ከሚጠበቁ የልህቀት ተቋማት አንዱ መሆኑን ተናግረዋል።

የዩኒቨርሲቲውን የ2018 በጀት ዓመት የሥድስት ወራት የሥራ ክንውን ሪፖርት ለቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት ፕሬዝደንቱ ኢንጅነር ዶ.ር. አብደላ ከማል፣ ዩኒቨርሲቲው ወደ ራስ ገዝነት ለመሸጋገር የሚያስችለውን በዳይሬክተር የሚመራ ልዩ ቢሮ በማቋቋም፤ የ10 ዓመት ፍኖተ- ካርታ በመቀረፅ 28 የሚደርሱ መመሪያዎችን እና ፖሊሲዎችን ማዘጋጀቱን አንስተው፣ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ለመሆን 96 በመቶው ዝግጅት መደረጉን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አስረድተዋል ተብሏል።



*የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲው ጉብኝት በከፊል፤*

## 3. የውክልና ሥራዎች

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው መጋቢት ወር፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ካሉባቸው ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶች መካከል አንዱ የሆነውን ከወርኃ የካቲት የቀጠለውን የውክልና ሥራቸውንም ሰፋ አድርገው አከናውነዋል። በዚኽም፣ ሃያ ስምንት የሚደርሱ እንደራሴዎች ወደ'ምርጫ ክልሎቻቸው በመሄድ ከመራጮቻቸው ጋር፣ በአገራዊ እና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ሲመክሩ ወሩን አገባደዋል። በዚኽም፣ ወደ ቤንሻንጉል/ጉሙዝ ሦሥት፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አንድ፣ ኦሮሚያ ዐሥራ ሰባት፣ ሱማሌ አንድ፣ ድሬዳዋ አንድ እንዲኹም ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አምስት እንደራሴዎች ከወከሏቸው ማህበረሰቦች ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡

### 3.1 **የቤንሻንጉል/ጉሙዝ መራጮች ምን ጉዳዮችን አነሱ**?

በወርኃ መጋቢት በተከናወነው የእንደራሴዎቹ ሕገ-መንግሥታዊዉ የውክልና ሥራ ከተጎበኙት ክልሎች መካከል አንዷ ቤንሻንጉል/ጉሙዝ ስትሆን፣ በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚው ደራሽ የነበሩት **የተከበሩ ወ/ሮ ባይታ ባውዴ** ነበሩ፤ 'ርሳቸውም፣በመተከል ዞን ዳንጉር ወረዳ አይፖፑ ቀበሌ በሰላም፣ በልማት እና በምርጫ ዝግጅት ሥራዎች ዙሪያ ከቀበሌው ማኅበረሰብ ጋር ተወያይተዋል።

ወደዚያ ክልል የሄዱት በምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው **የተከበሩ ሙባረክ ኤልያስም፣** በመንጌ ወረዳ ተገኝተው ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ አካሂደዋል። እንደራሴውም፣ የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ አቅም ለማሳደግ መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ለመራጮቻቸው መናገራቸው ሲሰማ፤ **የተከበሩ ወ/ሮ መናሂል ኢምራን** ደግሞ፣ በአቡራሞ ወረዳ በነባር ኮምሽጋ ማዕከል ከሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር በአከባቢው የመልካም አሥተዳደር እና አገልግሎት አሰጣጥ፣ በፀጥታ እና ሠላም፣ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና በልማት ሥራዎች ዙሪያ ከመረጮቻቸው ጋር ተወያይተዋል ተብሏል።



*የቤንሻንጉል/ጉሙዞ የውክልና ሥራ በከፊል፤*

### 3.2 **ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ**...

ከፌዴሬሽኑ አዲስ አባላት መካከል አንዷ የሆነችው ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያም፣ በዚኽ ወር የውክልና ግብር ከተከናወናባቸው መካከል አንዷ ነበረች። እንደ እንደራሴዎች ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነም፣ **የተከበሩ እሸቱ ገ/ማሪያም** በዲዚ ልዩ የምርጫ ክልል በቤሮ ወረዳ በጋቢሳ ቀበሌ ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በኢኮኖሚ፣ በልማት፣ በሰላም እና ደኅንነት ዙሪያ ውይይት አድርገዋል፤ 'ርሳቸው፣ የአከባቢውን ሰላም እንዴት ማስጠበቅ እንደሚገባ ብቻም

ሳይሆን፣ 7ኛው አገራዊ ምርጫ ሰላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች መሰራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል ተብሏል።



*በዲዚ ልዩ የምርጫ ክልል የተካሄደው የውክልና ሥራ በከፊል፤*

## 3.3 የኦሮሚያ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች

በዚኽኛው የውክልና ወቅት፣ በዛ ያሉ የውክልና ሥራዎች ከተካሄደባቸው ክልሎች መካከል ቀዳሚዋ ኦሮሚያ እንደነበረች፣ ከምክር ቤቱ የተሰባሰቡት ውክልና ተኮር መረጃዎች ይጠቁማሉ። በክልሉ በጅማ ዞን ዴዶ ወረዳ የተካሄደውን የመራጭ-ተመራጭ ውይይት የመሩት **የተከበሩ ወ/ሮ አይሻ ሼህሺፋ** መሆናቸው ሲጠቀስ፣ ‘ርሳቸውም፣ በሰላም፣ በኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ፣ በመሠረተ-ልማት ዝርጋታ፣ በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ባለፋት አምስት ዓመታት የተሰሩ ሥራዎች እንደ አገር እና እንደ ወረዳ የተመዘገቡ ስኬቶችን ገለፃ አድርገዋል ተብሏል።

ወደ ምዕራብ ሀረርጌ ዞን ዶባ ወረዳ ብቅ ያሉት እንደራሴው **የተከበሩ ጁሀር መሀመድ፣** የኅብረተሰቡ ጥያቄ ትክክል መሆኑን ገልፀው፣ መንግሥት ከሕዝብ ለሚነሱ የመሠረተ-ልማት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በቁርጠኝነት እንደሚሰራ አስረድተዋል። ጅማ የነበሩት ሌላይኛዋ እንደራሴ **የተከበሩ ወ/ሮ ለጢፋ አባሳምቢ፣** በዓመት ኹለት ጊዜ የወከልነውን ሕዝብ በማወያየት ከሕዝቡ የሚነሱ ጥያቄዎችን እና ቅሬታዎችን ለሚመለከተዉ አካል በማድረስ እና በመከታተል የልማት ጥያቄዎች እንዲፈቱ በትኩረት እየሰራን ነው ብለዋል ተብሏል። ከክልሉ ከተሞች አንዷ ወደሆነችው ሸገር ከተማ የተጓዙት **የተከበሩ አዲሷ አሰፋ** በመሩት የመራጭ-ተመራጭ መድረክ ላይ ደግሞ፣ ከቡራዩ፣ ከገፈርሳ ጉጄ እና መልካ ኖኖ ክፍለ ከተሞች የተውጣጡ የሃይማኖት አባቶች፣ አባ ገዳዎች፣ አደ ሲቄዎች፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች እና ነዋሪዎች መሳተፋቸው ተዘግቧል።

አርሲ ዞን ጮሌ ወረዳ ጮሌ ምርጫ ክልል የደረሱት **የተከበሩ ወይዘሮ ዘውድነሽ ቱሉ** በበኩላቸው፣ ባለፉት የለውጥ ዓመታት ከሕዝቡ ሲነሱ የነበሩ የመሠረተ-ልማት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ መንግስት ከምንጊዜውም በላይ በትኩረት እየሰራ መሆኑን መናገራቸው ሲጠቀስ፤ ወደዚያው ዞን ሙኔሳ ወረዳ ለመሰል የውክልና ሥራቸው የተጓዙት **የተከበሩ ወ/ሮ ማርታ ለማ፣** በባለፉት ዓመታት ሕዝቡ ያቀረባቸውን የመሠረተ-ልማት ጥያቄዎች መንግስት በቁርጠኝነት እየመለሰ እንደሆነ መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

በወርጎ መጋቢት አጋማሽ ወደ ጅማ ዞን መንቻ ወረዳ የተጓዙት **የተከበሩ ወ/ሮ ጫልቱ ሞሐመድ** በበኩላቸው፣ በአገር ደረጃ እየተከናወኑ ያሉ ፕሮጀክቶች በኮሪደር ልማት፣ በሕዳሴ ግድብ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ የሚወጡ ሕጎች፣ የተቋማት ማሻሻያ እና የማዘመን ሥራ እንዲኹም በቴክኖሎጂ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ለመራጮቻቸው ገልጸዋል ተብሏል።

በምሥራቅ ወለጋ ዞን በሳስጋ ወረዳ በቶኩማ ፅጌ ክላስተር እና በጋሎ ክላስተር የተካሄደውን የመራጭ ተመራጭ ወይይት ለመሩት **የተከበሩ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ እጅጉ፣** ኅብረተሰቡ የመንገዱን ግንባታ ለማስተጓጎል የሚሰሩ የጥፋት ኃይሎችን ለመከላከል ከፀጥታ አካላት ጋር በመሆን ጥበቃ እንደሚያደርግ ቃሉን ሰጥቷቸዋል ተብሏል።

በኦሞ በየም ወረዳ የነበረውን የመራጭ-ተመራጭ መድረክ የመሩት **የተከበሩ ወ/ሪት ፋይማ ሼክ ጀማል፣** በመንግስት እና በሕዝብ መካከል ያለው መግባባት እንዲጠናከር ከሕዝቡ ጋር የሚደረጉ ውይይቶች አስፈላጊ መሆናቸውን ከመግለጻቸው ባለፈ፣ መንግስት በልማት፣ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካ እና በኢኮኖሚ ዘርፎች እየሰራ ያለው ሥራ ለሕዝቡ ተስፋ የሚሰጥ መሆኑን መናገራቸው ተሰምቷል።

በግራር ጃርሶ ምርጫ ክልል የተካሄደውን የመራጭ-ተመራጭ ውይይት የመሩት የምርጫ ክልሉ ተወካይ **የተከበሩ መሰረት ሽፈራው** እንደነበሩ ሲዘገብ፤ የምሥራቅ ወለጋ ዞን ጅማ አርጆ ወረዳ ትቤ ጫፌ ቀበሌው የመራጭ ተመራጭ ውይይት ደግሞ፣ የዚያው ምርጫ ክልል ተወካይ **የተከበሩ ዶ.ር. ቡዙአየሁ ደገፌ** መሆናቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል።



*ከኦሮሚያው የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች መካከል፤*

ባለፉት አምስት ዓመታት የተከናወኑ የልማት ሥራዎች፣ የተመዘገቡ ስኬቶች እና የተገኙ ውጤቶች ውጤታማ መሆናቸውን የተናገሩት ደግሞ፣ ሊሙ ሰቃ እና ኖኖ ቤንጃ ወረዳዎች ደርሰው ሕዝቡን ያወያዩት **የተከበሩ ወ/ሮ ሚራጅ ዘኪይ ጀማል** ሲሆኑ፤ ቡኖ በደሌ ዞን በመኮ ሣቺ ምርጫ ክልል ደርሰው የነበሩት **የተከበሩ ፍቃዱ ሞሲሳ፣** በመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረኩ፣ መንግስት የሕዝቡን የመሠረተ-ልማት ጥያቄ ለመመለስ እያደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ከመራጮቻቸው ተነስቶላቸው ነበርም ተብሏል።

በክልሉ በሚገኘው ባሌ ዞን ሮቤ ከተማ ጎባ ክፍለ ከተማ በነበረው የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ ለተገኙት **የተከበሩ ኡስታዝ ካሚል፣** የመንገድ፣ የመጠጥ ውኃ፣ የኔትወርክ እና የመብራት መቆራረጥ እና ተደራሽነት፣ ሥራ አጥነት እና የኑሮ ውድነት የሚሉት ጥያቄዎቹ መራጮቻቸው ካነሱላቸው ጥያቄዎች መካከል ዋንኞቹ ነበሩ።

**የተከበሩ ወ/ሮ ፈሪዳ ሸምሱድን** እና **የተከበሩ ዶ/ር ኤልያስ አህመድ** በበኩላቸው፣ በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን በደደር ወረዳ እና ከተማ አሥተዳደር ተገኝተው፣ ከመራጮቻቸው ጋር በልማት እና በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ማካሄዳቸው ሲዘገብ፤ **የተከበሩ ወ/ሮ ብርቄ ባሕሩ** ደግሞ፣ ሰሜን ሸዋ ደብረ ሊባኖስ እና ያያ ጉለሌ ወረዳ ደርሰው ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በሰላም እና በልማት ጉዳዮች ዙሪያ መወያየታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል።

## 3.4 **ከሱማሌስ?**

የምሥራቋ የአገሪቷ ክፍል ሱማሌ፣ በዚኹ መጋቢት ወርም የውክልና ሥራዎችን ከተመለከቱት ክልሎች መካከል አንዷ ነበረች። አራቢ ምርጫ ክልል ቶግ ውጫሌ ከተማ የደረሱት **የተከበሩ ከማል ሃሺ፣** ከመራጮቻቸው ጋር በነበራቸው የመራጭ-ተመራጭ መድረክ፣ የቶግ ወጫሌ ከተማ የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ የቆየ ቢሆንም የውኃ ጉድጓዶቹ የኢነርጂ ግብዓት ስላልተመቻቸላቸው የፕሮጀክቱ የበላይ አካል የሆነው የኢፌዴሪ የውኃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና የሚመለከተው አካል ሁሉ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ አሳስበው ነበር ተብሏል።

## 3.5 **ድሬዳዋ ምን አነሳች?**

የፌዴሬሽኑ ኹለተኛ የከተማ መሥተዳደር የሆነችው ድሬዳዋም፣ የመጋቢት ወርን የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ ከተካሄደባቸው መካከል ትገኝበታለች። አስቀድሞ ወደ ከተማይቱ የደረሱት **የተከበሩ ዶ.ር. ቢፍቱ መሀመድ** በመሩት የመራጭ-ተመራጭ መድረክ የነበሩት ተሳታፊዎች ከመንገድ እስከ የፍሳሽ ማስወገጃዎች መደፈን፣ ከሥራ ዕድል እስከ የኑሮ ውድነት የደረሱ ቢፈቱ ይበጃሉ ያሏቸውን ጥያቄዎች አንስተውላቸዋል ተብሏል። ‘ርሳቸውም፣ በአሥተዳደሩ አቅም በአፋጣኝ ምላሽ ለሚሹ ችግሮች ከአሥተዳደሩ ጋር በመወያየት በአፋጣኝ መፍትሔ እንዲሰጣቸው እንደሚደረግ ገልፀዋል።



*የተከበሩ ዶ.ር. ቢፍቱ መሀመድ፣ በውክልና ሥራቸው ወቅት፤*

## 3.6 **ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የተሰሙት**

ሌላይኛዋ ደቡባዊ የአገሪቷ ክፍል ደቡብ ኢትዮጵያ ክልልም፣ በዓመቱ ሰባተኛ ወር የተካሄደው የውክልና ሥራ ከጎበኛቸው ክልሎች አንዷ እንደነበረች ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የወጣው መረጃ ይጠቁማል። በቀዳሚነት በክልሉ ወደሚገኘው ጌዴኦ ዞን ቡሌ ምርጫ ክልል የደረሱት **የተከበሩ ግዛቸው አየለ** በነበራቸው የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ፣ ‘ርሳቸው አባል የሆኑበት የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት እና የፌደራሉ መንግስት አማካኝነት፣ ባለፉት ስድስት ወራት እና አምስት ዓመታት

ውስጥ የተሰሩ አንኳር ሥራዎችን ለመድረኩ ተሳታፊዎች አስረድተዋል ተብሏል።

ወደ ወላይታ ዞን ቦዲቲ ከተማ አሥተዳደር የደረሱት **የተከበሩ ወ/ሮ መቅደስ ደስታ**ም እንዲኹ፣ ባለፋት ስድስት ወራት በምክር ቤቱ እና በአገር ደረጃ የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎችን እና የተገኙ ወጤቶችን በተመለከተ ላገኟቸው መራጮቻቸው ማብራሪያ መስጠታቸውን ዘገባው ሲጠቅሳቸው፤ ጌዲኦ ዞን ወናጎ ወረዳ እና ከተማ አሥተዳደር ለመሰል የውክልና ሥራ ብቅ ያሉት **የተከበሩ ወ/ሮ አስቴር በሽር** በበኩላቸው፣ እንደራሴዎቹ በዓመት ኹለት ጊዜ ወደ 'የምርጫ ክልላቸው በመውረድ ከወከላቸው ማኅበረሰብ ጋር በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ዘርፎች የሚነሱ ችግሮችን እና የሕዝቡን ጥያቄዎች በመሰብሰብ እንደሚመክሩ ተናግረዋል ተብሏል።

**የተከበሩ ኢንጂነር አልማዝ አሳሌ** ደግሞ፣ ወደ ወላይታ ዞን ቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ ደርሰው ከመራጮቻቸው ጋር መወያየታቸው ሲጠቀስ፣ አሪ ዞን ዎባ አሪ ወረዳ የነበሩት **የተከበሩ ዶ.ር. ወልደየስ ደበበ** በበኩላቸው፣ ሕዝቡ ያነሳቸው ጥያቄዎች ተገቢነት ያላቸው እና በመንግስት በኩልም ትኩረት እንዲሰጣቸው ለሚመለከተው አሥፈጻሚ አካላት በማድረስ ለተፈጻሚነቱ ክትትል እንደሚያደርጉ ለመድረኩ ተሳታፊዎች መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች መካከል፤*

## 4. የፓርላማው ዲፕሎማሲ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ባሳለፍነው መጋቢት ወር ካከናወኗቸው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎች መካከል አንዱ፣ **ሴት እንደራሴዎቹን ለሥልጠና እና ለልምድ ልውውጥ በሚል ወደ አገረ-ሕንድ የላከበት ኹነት** ነበር። በምክትል አፈ-ጉባኤዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ የተመራ የኢትዮጵያ ሴት ከፍተኛ አመራሮች ልዑካን ቡድን ሲሆን፣ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ በመርሃ ግብሩ እንደገለጹት፣ የሴቶች ቀን ሲከበር በኹሉም ዘርፍ የተሳትፎ እና የተጠቃሚነት ጉድለቶች መታረማቸውን እና ለውጥ መምጣቱን እየፈተሹ ለመሄድ ያግዛል ብለዋል ተብሏል።



*ሠልጣኞቹ ሴት እንደራሴዎች በሕንድ፤*

የሥልጠናው እና የልምድ ልውውጥ ጉብኝቱ፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተለይም ደግሞ በኅብረት ሥራ ማኅበር በመደራጀት ከትንሽ ተነስተው ትልልቅ ተቋማትን እና ፋብሪካዎችን በመገንባት የቤተሰብ ብልጽግናን ለማረጋገጥ፣ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር እንዲኹም የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን በማዳበር ለአገራዊ ዕድገት እያበረከቱት ባለው አስተዋጽዖ ላይ ተሞክሮ ለመቅሰም እና የኢትዮጵያ እና የሕንድ ግንኙነትን ለማጠናከር ያለመ እንደነበር መጠቆሱን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያሳያል። በተያያዘ በሥልጠናው የተሳተፉ ሴት አመራሮች ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀንን ሕንድ አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በድምቀት አክብረዋል።

ሌላይኛው የወሩ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ **የኢትዮጵያ እና የቻይናን ባለብዙ ዘርፍ ግንኙነት** ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የተነገረበት ኹነት ነበር። ይኽ ኹነትም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከቻይና መንግስት ልዑካን ጋር የተወያየበት ሲሆን፣ በውይይቱም የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ እና ሠላሳ ዓመታት ባካሄደችው የመሠረተ-ልማት ግንባታ ሂደቶች ከቻይና መንግስት የልማት እንቅስቃሴ ጋር የተቆራኘ መሆኑን ጠቁመው፣ በቀጣይም ይኽ ትስስር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀዋል ተብሏል።

ሌሎቹ የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ የቻይናን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በማጣቀስ በጤና ዘርፍ ቻይና ኢትዮጵያ ላይ መሥራት ያቀደችው ሥራ ካለ እና የቻይና አፍሪካ ትስስርን መሰረት በማስያዝ ረገድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ታሪካዊ ሚናን አውስተው በአቪዬሽን ዘርፍ ስላላት መሰናዶ ጥያቄ ማቅረባቸው ተዘግቧል። የቻይናው ልዑክ ቡድን መሪው ሱን ሚንግዚ በበኩላቸው፣ ጤናን መሰረት ያደረገ ሰው ሰራሽ አእምሮ ለሰፊው ማኅበረሰብ ጥቅም በአማርኛ ለማልማት ዕቅድ መያዙን ገልፀዋል።

ከዚኽ ባለፈም፣ የቻይና አቬዬሽን እና የጠፈር እንቅስቃሴዎችን የማስተሳሰር እቅድ ሳተላይት ያመጠቀችውን እና የአቬዬሽን ዘርፏን በአህጉር ዓቀፍ ደረጃ መሪ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰች ላለችው ኢትዮጵያ የሚያበረክተው ረብ ይኖራል ተብሎ ተስፋ መኖሩም በውይይቱ መመላከቱን ከምክር ቤቱ የወጣው ዘገባ ያሳያል።



*የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከቻይና መንግስት ልዑካን ጋር፤*

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ከሌላይኛው የቻይና ልዕካን ጋር የተወያዩበት ኹነትም ሌላው የወሩ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ነበር። **ከቻይና ብሔራዊ ሕዝባዊ ኮንግረስ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሊቀ-መንበር ዌይ ሁዋን ጋር በኹለትዮሽ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ የተወያዩት አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣** ኢትዮጵያ እና ቻይና ለዘመናት የዘለቀ ጠንካራ የኹለትዮሽ ስትራቴጂካዊ ግንኙነት ያላቸው አገራት መሆናቸውን በመጥቀስ፣ በወንድማማችነት እና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተው ይኽ የአገራቱ ዲፕሎማሲያዊ ትስስር በፈተና ወቅቶች ሳይበገር የዘለቀ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።

በአኹኑ ወቅት የቻይና ባለሀብቶች በኢትዮጵያ የሚያፈሱት መዋዕለ-ንዋይ እያደገ መምጣቱን ያነሱት አፈ-ጉባኤው፣ ይኽም በማኑፋክቸሪንግ፣ በመሠረተ-ልማት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ እና በተለያዩ መስኮች ተጠቃሚ ማድረጉን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል ለምታደርገው ጥረትም፣ ቻይና ድጋፏን እንድትሰጥ አፈ-ጉባኤው ጥሪ ማቅረባቸው ተጠቅሷል። የቻይና ብሔራዊ ሕዝባዊ ኮንግረስ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሊቀ-መንበር ዌይ ሁዋን በበኩላቸው፣ የኢትዮ-ቻይና ጠንካራ ወዳጅነት በመከባበር ላይ የተመሰረተ፣ አስተማማኝ እና ትልቅ የወደፊት ራዕይን የሰነቀ ነው ብለዋል።

ቻይና ከአፍሪካ ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ጠንካራ እና ፍሬያማ እንዲሆን የኢትዮጵያ ሚና ትልቅ መሆኑን ያነሱት ሊቀመንበሩ፣ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል የጀመረችውን ጉዞ ቻይና እንደምትደግፍም አረጋግጠዋል ተብሏል።



*የቻይና ብሔራዊ ሕዝባዊ ኮንግረስ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሊቀ-መንበር ዌይ ሁዋን እና አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፤*

**የኢትዮጵያ እና የአርሜንያ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት** ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የተነገረበት ኹነትም፣ የወሩ አንዱ

ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ነበር። አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ የአርሜኒያ አምባሳደር ሳሃክ ሳርጊሲያን በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት፣ በንግድ፣ በፋይናንስ እና በትምህርት ዘርፍ ልምድ ለመለዋወጥ በሚያስችሏቸው ጉዳዮች ላይ ብቻም ሳይሆን፣ የኹለቱን አገራት የእንደራሴዎች ምክር ቤት ግንኙነት ለማጠናከር እና በዓለም ዓቀፍ እና አህጉራዊ መድረኮች ለመተባበር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል ተብሏል።

አፈ-ጉባኤው፣ የኢትዮጵያ እና የአርሜኒያ የኹለትዮሽ ትስስር ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረ እና ታሪካዊ መሆኑን ጠቀመው፣ ይኽንን ግንኙነት በይበልጥ ማጠናከር ይገባል ብለዋልም ተብሏል። በኢትዮጵያ የአርሜኒያ አምባሳደር ሳሃክ ሳርግሲያን በበኩላቸው፣ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዘመናትን ያስቆጠረ ታሪካዊ ግንኙነት እና ወዳጅነት በቀጣይ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ቁርጠኛ መሆኗን ተናግረዋል።

የአርሜኒያ ባለሀብቶችም በኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ ዘርፍ በተለይም በቴሌኮም ያላቸውን ልምድ በመጠቀም በዘርፉ ለመሰማራት የመዋዕለ-ንዋይ እድሎችን በመመልከት ከኢትዮጵያ መንግስት እና ከዘርፉ ተዋናዮች ጋር ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት መኖሩን መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*አፈ-ጉባኤው የአርሜኒያው አምባሳደር ሳሃክ ሳርጊሲያን ጋር ሲወያዩ፤*

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **ከአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ አባል የተከበሩ ቲዬሪ ማሪያኒ** ጋር በአገራዊ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ ያካሄደው ውይይትም፣ እንዲኹ የወርኃ መጋቢት ሌላው የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውን ነበር።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ኢትዮጵያ በታሪክ አጋጣሚ የባሕር በር ማጣቷን ገልፀው፣ በአኹኑ ወቅት እያስመዘገበችው ካለው የኢኮኖሚ እና የሕዝብ ቁጥር ዕድገት አንጻር የራሷ የባሕር በር መኖር ጉዳይ ወሳኝ መሆኑን አብራርተዋል። ሰብሳቢው አክለውም፣ ኢትዮጵያ ይኽንን ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ እና በስምምነት ለመፍታት ጥረት እያደረገች መሆኑን እና ጎረቤት አገራትም ለዚህ አዎንታዊ ምላሽ እንደሚሰጡ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል ተብሏል።

የውይይት መድረኩ በአውሮፓ እና በኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤቶች፣ እንዲኹም በፈረንሳይ እና በኢትዮጵያ ምክር ቤቶች መካከል ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑንም የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ጠቅሰዋል። የአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ አባል ቲዬሪ ማሪያኒ በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ጥያቄ ወቅታዊ፣ ታሪካዊ እና በምክንያት ላይ የተመሰረተ ነው ብለዋል።

በ1950ዎቹ በተባበሩት መንግሥታት የነበረውን የታሪክ ሃይትን ያስታወሱት ቲዬሪ ማሪያኒ፣ የኢትዮጵያን ፍላጎት

ለማሳካት አስፈላጊውን ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋልም ተብሏል።



*የአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ አባሉ ቲዬሪ ማሪያኒ፣ ከየውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው ጋር በተወያዩበት ወቅት፤*

## 5. እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው

### 5.1 ዓለም ዓቀፉ የሴቶች ቀን

ወሩ መጋቢት እንደመሆኑ፣ ሴት እንደራሴዎቹ በ'የዓመቱ መጋቢት 4 ቀን የሚከበረውን **ዓለም ዓቀፉን የሴቶች ቀን** አክብረው ውለዋል። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት አመራሮች እና ሠራተኞች በተገኙበት ዓለም ዓቀፉ የሴቶች ቀን (አልያም በተለምዶ አጠራሩ 'ማርች 8')፣ "የሴቶች ድምጽ ለእኩልነት እና ለበለጸገች ኢትዮጵያ" በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ዝግጅቶች መከበሩን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷል።

በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የዋና ጸሓፊ ተወካይ እና የአሥተዳደራዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሓፊ አቶ ከረዩ ባናታ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሴቶች ለመብታቸው እና ለእኩልነታቸው ያደረጉትን ትግል የምንዘክርበት እና የምናስቀጥልበት ቀን ነው ሲሉ በመክፈቻ ንግግራቸው ላይ አንስተዋል። የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ባለሙያዋ ወ/ሮ ኂሩት እንቢያለ፣ ቀኑ ለሴቶች እውቅና እና ክብር ለመስጠት የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር ሴቶች በማንኛውም አገራዊ ጉዳይ ላይ እኩል ተሳትፎ እንዳይኖራቸው እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮችን ለመመርመር እና መፍትሔ ለመፈለግ የሚያበረታታ መሆኑን በሥልጠናው ላይ አንስተዋል ተብሏል።

በመድረኩም የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ሙያዊ ድጋፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሓፊ ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻ እና አንድነት አድነው የመንግስት ተጠሪ ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊን ጨምሮ ሌሎች የጽሕፈት ቤቱ አመራሮች እና ባለሙያዎች መገኘታቸውን ዘገባው ጠቅሷል፤ (በዚኹ በዓል መነሾነት የቀረበውን የብሪጅን ዳሰሳዊ ምልከታ በገጽ 43 ይመለከቷል)።

### 5.2 የምርምር ሥራ ምክክር መድረክ

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **"የፓርላማው ሚና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አፈፃፀም፣ ውጤታማነት እና ለኢትዮጵያ አገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ ያላቸው አስተዋፅኦ"** በሚል ርዕስ የምርምር ሥራ ምክክር መድረክ መካሄዱ ደግሞ፣ ሌላይኛው የወሩ የእንደራሴዎቹ የ'ራስ በ'ራስ ክንውን ነበር። ምርምሩም፣በቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመን ሆልዲንግ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነበር ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ አገር በቀል ኢኮኖሚውን በማሳደግ ረገድ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን ሲያነሱ፤ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጅነር ስለሽ ኮሬ በበኩላቸው፣ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ስር የሚገኙ ድርጅቶች ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ አፈፃፀም ላይ ያሉ በመኖራቸው ወደ አንድ ለማምጣት እንደ አገር ትኩረት ተሰጥቶ የማሻሻያ ሥራ መሰራቱን አንስተዋል ተብሏል።



*የምክክር መድረኩ በከፊል፤*

## 5.3 የውክልና ሥራ ላይ የተካሄደ ውይይት

በዚኹ ወርኃ መጋቢት በእንደራሴዎቹ ከተከናወኑት ዓበይት ተግባራት መካከል ሌላው፣ **የውክልና ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራቸውን አስመልክቶ የተካሄደው ኹነት** ነበር። እንደ ምክር ቤቱ ዘገባ፣ የክልል የውክልና ሥራ አስተባባሪዎች በውክልና ሥራ የተነሱ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን ለምክር ቤቱ አቅርበው ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል። ውይይቱን የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ የመሩት ሲሆን፣ አስተባባሪዎቹ ከመራጩ ሕዝብ ጋር ባደረጉት ተከታታይ ውይይቶች የሰበሰቧቸውን መሠረታዊ ጥያቄዎችን በየተራ አቅርበዋል ተብሏል።

አስተባባሪዎቹም፣ በውይይቱ ወቅት በመንግስት በኩል እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎችን፣ በእንደራሴዎቹ በኩል የሕዝብን ጥያቄዎች ለማዳመጥ እየታየ ያለው ቁርጠኝነትን እና ሕዝብ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በመንግስት በኩል እየታየ ያለውን ቁርጠኝነት በጥንካሬ ካነሷቸው ነጥቦች ውስጥ ተጠቃሽ መሆናቸውን ማንሳታቸውን ዘገባው ጠቅሷል።በአስተባባሪዎች በኩል የቀረቡ የሕዝብ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች በሚመለከታቸው አሥፈፃሚ ተቋማት በኩል ተገቢውን ምላሽ እና ተግባራዊ መፍትሔ እንዲያገኙ ለማድረግ ልዩ የክትትል ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባም አስተባባሪዎቹ ጠይቀዋል።

በመድረኩ ላይ ሪፖርታቸውን ያቀረቡት የሲዳማ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የአፋር፣ የቤኒሻንጉል/ጉምዝ፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች እንዲኹም የድሬዳዋ እና የአዲስ አበባ ከተማ አሥተዳደር የውክልና ሥራ አስተባባሪዎች እንደነበሩም ዘገባው አስታውሷል።



*የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ፣ የውይይት መድረኩን ሲመሩ፤*

## 5.4 የሥልጠና መድረክ

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባዔ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት በሥራ እድል ፈጠራ ዘርፉ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ወሳኝነት እንዳለቸው የተናገሩበት መድረክም፣ የወሩ የእንደራሴዎቹ ኹነት ነበር። አፈ-ጉባዔዋ ይኽንን የገለጹት፣ **'ለሕዝብ**

**አመራር እና ለወደፊት ዝግጁነት 'ራስን ማግኘት'** በሚል ርዕሰ-ጉዳይ፣ በሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር አማካኝነት ለአንደራሴዎቹ በተሰጠው የሥልጠና መድረክ ላይ ነው ተብሏል።

ሥልጠናው፣እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ እናየላቀ አገራዊ ኢኮኖሚ ለማስመዝገብ፣ ትውልድን ለማሻገር እና አገራዊ ተልዕኮን በብቃት ለመወጣት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለውም አፈ-ጉባኤዋ አስገንዝበዋል። ፈተናዎችን ተቋቁሞ ወደ መልካም ዕድል ለመቀየር ይኽ ሥልጠና ፋይዳው የጎላ መሆኑን የገለጹት የተከበሩ ሎሚ፣ ሥልጠናውን በብዝሓ-ዘርፍ ማየት እንደሚያስፈልግም አሳስበዋል ተብሏል።

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ሚንስትሯ የተከበሩ ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ያሏት እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ እና ኢኮኖሚው የበለጠ እንዲጎለብት እንዲኽ ዓይነት ሥልጠናዎች አስፈላጊ መሆናቸውን አስገንዝበዋል ተብሏል።



*'ለሕዝብ አመራር እና ለወደፊት ዝግጁነት 'ራስን ማግኘት' የተሰኘው ሥልጠና በከፊል፤*

## 6. እንደራሴዎቹ እና ምርጫ 2018

ተሰናባቹ 6ኛው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ምርጫ 2018ን አስመልክቶ የተለያዩ ክንዋኔችን በዚኹ መጋቢት ወርም ከውኗል። ከእነዚኽ መካከል አንዱም፣ **ዜጎች የምርጫ ካርድ በማውጣት ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን በአግባቡ መጠቀም እንዳለባቸው** ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ወ/ሮ ሎሚ በዶ ያሳሰቡበት ነበር። የመምረጥ እና የመመረጥ የዜጎች ሕገ-መንግሥታዊ መብት ነው ያሉት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ፣ ምርጫው ነጻ፣ ገለልተኛ፣ ሰላማዊ እና በሕዝብ ዘንድ ተዓማኒነት ያለው እንዲሆን ኹሉም አካል የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበትም አስገንዝበዋል ተብሏል።

የተከበሩ ሎሚ ይኽን ያሉት፣ በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ዱግዳ መቂ ንዑስ ጣቢያ የምርጫ ካርድ ባወጡበት ዕለት መሆኑንም የምክር ቤቱ ዘገባ አስታውሷል።



*ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ የምርጫ ካርድ ባወጡበት ወቅት፤*

## 7. ኢትዮጵያ ምን ተስማማች?

በወርኃ መጋቢት፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የተለያዩ የብድር ስምምነቶችንም አጽድቀዋል። እንደራሴዎቹ፣ በ6ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 12ኛ መደበኛ ስብሰባቸውን ሲካሄዱ፣ **በኢፌድሪ እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል** የተደረገውን የብድር ስምምነት በሙሉ ድምጽ አጽድቀዋል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ የረቂቅ ዐዋጁን ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡ ሲሆን፣ በብድር የተገኘውን ገንዘብ የህክምና ተቋማትን በተሟላ ግብዓቶች በማደራጀት የህክምና መሳሪያዎች ችግርን ለመፍታት፣ የጤና አገልግሎቱን ለማሻሻል እንዲኹም የአቅርቦቱን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት መንግስት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በተለይም ከለጋሽ አገራት፣ ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች እና ከሌሎች የጤና ድጋፍ ሰጪ አጋሮች ጋር በትብብር በመሥራት የተቀናጀ የጤና ስርዓት በመዘርጋት ለኅብረተሰቡ የተሻለ የጤና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።

ከዚኽ ባለፈም፣ በስምምነት የተገኘው ይኽ የብድር ገንዘብ ቀለል ያለ ወለድ የሚከፈልበት እና ዐሥራ አምስት ዓመታት የችሮታ ጊዜ ያለው እና በአርባ ዓመታት ውስጥ የሚከፈል መሆኑ፣ ከአገሪቷ የብድር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሰብሳቢው አክለው መናገራቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል። እንደራሴዎቹም፣ ረቂቅ ዐዋጁ ዐዋጅ ቁጥር 1406/2018 ሆኖ በሙሉ ድምጽ ይጸድቅ ዘንድ ፈቃዳቸው ሆኗል።

በዚያው 12ኛ መደበኛ ስብሰባ እንደራሴዎቹ የተመለከቱት ሌላይኛው የብድር ስምምነት፣ **በኢፌድሪ እና በዚኹ በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ** መካከል ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን ተጨማሪ የብድር ስምምነት ነበር። የተደረገውን ተጨማሪ የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ ዐዋጅ አጭር መግለጫ ያነበቡት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ሲሆኑ፤ እርሳቸውም፣ መንግስት የኤሌትሪክ ኃይል አቅርቦትን ማሟላት በአገራችን በኢንዱስትሪ፣ በግብርና እና ሌሎችም ዘርፎች እየተመዘገበ ያለውን ፈጣን ዕድገት ለማስቀጠል ያለውን ፋይዳ ይገነዘባል ብለዋል።

ከዚኽ አንጻርም፣ ለብሔራዊ ኤሌትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚሆን ከ60 ሚሊዮን በላይ የአሜሪካ ዶላር ተጨማሪ ቀላል ብድር ስምምነት ከባንኩ ጋር፣ የፌደራሉ መንግስት ጥቅምት 14 ቀን 2018 ዓ.ም. መፈራረሙን ጠቅሰዋል።

የብድር ስምምነቱም በዓመት 0.01 በመቶ ወለድ የሚከፈልበት ቢሆንም ቅሉ፣ አስፈላጊዎቹ ቀሳቁሶች ከኮርያ አቅራቢዎች የሚገዙ ከሆነ ከወለድ ነፃ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል ተብሏል፤ የአገልግሎት ክፍያው 0.1 በመቶ ለባንኩ ከመከፈሉ ባለፈ፣ የ15 ዓመታት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በአርባ ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ እንደሚጠናቀቅም

ተነግሯል። በመጨረሻም፣ እንደራዎቹ ረቂቅ ዐዋጁን ዐዋጅ ቁጥር 1407/2018 ሲሉ በሙሉ ድምጽ አጽድቀውታል።

እንደራሴዎቹ በዚኹ መጋቢት ወር በሦሥተኛነት ያጸደቁት የብድር ስምምነት፣ **በኢፌድሪ እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል** ለታዳሽ፣ የተቀናጀ፣ ዘላቂ ኃይል እና ዲጂታላይዜሽን ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የብድር ስምምነትን ነበር። ይኽንንም የውሳኔ ሐሳብ ለእንደራሴዎቹ በንባብ ያሰሙት፣ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ሲሆኑ፤ 'ርሳቸውም፣ የብድሩ መጠን 80 ሚሊየን ዩሮ መሆኑን ጠቅሰው፣ ብድሩም በየዓመቱ በ1.2 በመቶ ያህል የሚከፈል ሲሆን፣ 0.05 በመቶ ያክል የአገልግሎት ክፍያን እንደሚኖርም ተናግረዋል ተብሏል።

የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ፣ ብድሩ የሰባት ዓመታት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ፣ በ20 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ እንደሆነ ጨምረው ማንሳታቸው ተዘግቧል። እንደራሴዎቹም፣ረቂቅ ዐዋጁን ዐዋጅ ቁጥር 1408/2018 አድርገው በሙሉ ድምጽ አጽድቀውታል።

በዚኹ መደበኛ ስብሰባቸው እንደራሴዎቹ የተመለከቱት የወሩ ዐራተኛው የብድር ስምምነት፣ **በኢፌድሪ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል** ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔት እና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን ሦሥተኛ ተጨማሪ የብድር ስምምነትን ነበር። የዚኽንም የብድር ስምምነት የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ ሲሆኑ፣ የብድሩ መጠን 184 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር መሆኑን ጠቅሰው፣ ስምምነቱ ለአገሪቱ ወጣቶች የተሻለ የሥራ እድል ከመፍጠሩ ባለፈ ማኑፋክቸሪንግን የሚያጎለብት እንደሆነ ተናግረዋል።

ተጠሪ ሚኒስትሩ ለጥቀውም፣ ብድሩ ከወለድ ነጻ ሲሆን የስድስት ዓመታት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ30 ዓመታት ውስጥ የሚከፈል መሆኑን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። በብድር ስምምነቱ ዙሪያ የተወያዩት እንደራሴዎቹ ረቂቅ ዐዋጁን ዐዋጅ ቁጥር 1409/2018 አድርገው በሙሉ ድምጽ አጽድቀውታል።



*እንደራሴዎቹ ብድሮቹን ሲያጸድቁ፤*

## 8. የብሪጅ የሕግ ሥነ-ሐሳብ ዳሰሳዊ ምልከታ፦አዲሱ የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ለውጦች እና ሙግቶች፤

የኢትዮጵያ የፍትሕ ሥርዓት ለ65 ዓመታት ያህል ሲመራበት የቆየውን እና በ1954 ዓ.ም. በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የጸደቀውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ በመሻር፣ አዲስ ምዕራፍ ተቀላቅሏል። የማርቀቅ ሂደቱ ዐሥራ አምስት ዓመታት በላይ የፈጀው ይኸ ታሪካዊ ሰነድ፣ መጋቢት 24 ቀን 2018 ዓ.ም. በዋለው 13ኛው የኢፌድሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1410/2018 ሆኖ ጸድቋል። በአጠቃላይ 228 ገጾች እና 444 አንቀጾችን የያዘው ይኸ ሕግ፣ የተበታተኑ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግጋትን በአንድ ላይ በማጣመር የሕግ የበላይነትን ለማስፈን እና የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ለማክበር የተነደፈ ነው ተብሎም ተነግሯል። ከዚኽ አንጻርም፣ ብሪጅ በዚኽ ዐዋጅ ዙሪያ ለመወያያ ይሆን ዘንድ አጠር ያለ ዳሰሳ ማድረግን ሸታለች።

### የማሻሻያው ዳራ

የ1954ቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ የበይነ-መረብ፣ ድንበር ዘለል የፋይናንስ ሥርዓቶች እና ዘመናዊ የተደራጁ ወንጀሎች ባልነበሩበት ዘመን የወጣ ሕግ መሆኑ ይታወቃል። ያ ሕግ ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች መሠረታዊ መዋቅር የሰጠ ቢሆንም፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ግን ውስንነቶቹ ጎልተው ታይተዋል። በተለይም ስለ ማስረጃ ሕግ ያለው ዝምታ ትልቁ ጉድለቱ ተብሎ ሲጠቀስ ኖሯል። ኢትዮጵያ የተሟላ የማስረጃ ሕግ ስላልነበራት፣ ፍርድ ቤቶች በፍትሐ ብሔር፣ በወንጀል እና በባህላዊ ሕግጋት ውስጥ የተበታተኑ ድንጋጌዎችን ወይም የሮበርት ቢ. ሲድማንን ያልጸደቀ ረቂቅን ለመጠቀም ይገደዱ ነበር። ሕጉ ለ60 ዓመታት ሳይሻሻል የዘለቀ ቢሆንም፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤቱ ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ በረቂቅ ደረጃ ሲወያይበት እንደሰነበተ ተነግሯል። የጸደቀው ሕግ 195 ማሻሻያዎች ተደርጎለታል የተባለ ሲሆን፤ ከዚኽ ቀደም በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ሲነሱ የቆዩ ጉዳዮችን መልስ የሚሰጥ ነውም ተብሎለታል። ከዚያ ባለፈም ሕጉ፣ ይኽንን የሥድስት ዐሥርታት ክፍተት በመሙላት፣ ዘመናዊውን የወንጀል ውስብስብነት የሚፈታ፣ ቴክኖሎጂን ያገናዘበ እና ሰብዓዊ መብትን ማዕከል ያደረገ ሰነድ ሆኖ ቀርቧል በሚል በአርቃቂዎቹ ተወድሷል።

### አሚጊቹ አንቀጽ

አዲሱ ሕግ ምንም እንኳን በ253 ድጋፍ እና በኹለት ተቃውሞ ቢጸድቅም፣ ሂደቱ ጠንከር ባለ ሙግት የታጀበ ነበር። በዕለቱ የተገኙት 255 እንደራሴዎች ብቻ መሆናቸውን ተከትሎ፣ እንደራሴው ዶ.C. አበባው ደሳለኝ ምልዓተ ጉባኤ ሳይሟላ እና የትግራይ እንደራሴዎች በሌሉበት እንዲኽ ያለ ግዙፍ ሕግ መጽደቅ የለበትም የሚል ጠንካራ ተቃውሞ አቅርበዋል። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ከዚኽ ቀደም ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ ስብሰባውን ሰርዞ የነበረ ቢሆንም፣ በዕለቱ ግን አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ

ጫፉ ሕጉ ለሥድስት ዓመታት በጥንቃቄ የታየ መሆኑን በመጥቀስ መጽደቁ ተገቢ መሆኑን ገልጸዋል። ምልዕተ-ጉባኤውን አስመልክቶ ከተነሳው የሥነ-ሥርዓት ጥያቄ ባለፈ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አሥተዳደር ውስጥ በሚገኙ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ተቋማት እና ሠራተኞች ላይ የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን እንዲኖራቸው የሚፈቅደው አንቀጽ 25(3) ከፍተኛ ክርክር አስነስቶ ውሏል። እንደ ዶ.ር. ደሳለኝ ጫኔ ያሉ እንደራሴዎችም፣ “አንድ ክልል በሌላ ግዛት ላይ የዳኝነት ሥልጣን ሊኖረው አይገባም” የሚል የፌዴራሊዝም እና የመሬት ወሰንን የተንተራሰ ሙግት ቢያቀርቡም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሕግ እና የፍትሕ ቋሚ ኮሚቴ፣ ይኽ "ሕገ-መንግሥታዊ የልዩ ጥቅም መብት" መሆኑን በመጥቀስ ለተነሱት የተቃውሞ ድምጾች ምላሽ ሰጥቷል።

ክርክር ያስነሳው አንቀጽ 25 (3) ግን ምን ይላል? አንቀጹ፣ “በአዲስ አበባ ከተማ አሥተዳደር ውስጥ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተቋማት፣ ሰነዶች፣ በጀትና መሰል የክልሉ ጥቅሞች ላይ፣ በተቋማት ውስጥ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ፤ በክልሉ የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ አሥተዳደር ውስጥ ከሥራ ኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ በሚፈፅሙ ወንጀሎች ላይ የክልሉ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል” ሲል ይደነግጋል። አንቀጽ 25(3) በበኩሉ፣ “የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በክልሉ መንግስት ባለስልጣናትና ሠራተኞች ላይ ከኃላፊነታቸውና ከስራቸው ጋር በተገናኘ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ብቻ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው” በሚል የደነገገ ሲሆን፤ በአንቀጽ 25 (1/ረ) ስር ደግሞ “በፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣናትና ሠራተኞች ከኃላፊነት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ወንጀል” በፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር እንደሚወድቅ ተደንግጓል። እንደራሴዎቹ ዶክተራት የተከበሩ ዶ.ር. ደሳለኝ ጫኔ እና የተከበሩ ዶ.ር. አበባው ደሳለው፣ አንቀጹ የከተማዋን ራስን የማሥተዳደር መብት እና የሕግ የበላይነትን ይጋፋል በሚል እንዲወጣ ከመጠየቃቸው ባሻገር፣ “አንድ ክልል በሌላ ግዛት ላይ የዳኝነት ሥልጣን ሊኖረው አይገባም” የሚል መከራከሪያም አቅርበው ነበር። ከላይ ያነሳነው ቋሚ ኮሚቴውም፣ “ኦሮሚያ ክልል ፍትሕ ቢሮ ይዳኝ ያልነው በከተማዋ በሚገኙ የኦሮሚያ ክልል መስሪያ ቤቶቹ ቅጥር ግቢ የሚፈፀም ወንጀል ነው፤ ይኽም ሕገ-መንግስታዊ መብቱ ነው” ሲል ምላሽ ሰጥቷል። “ለአንዳንድ ጥያቄዎች ደግሞ ምላሽ አያስፈልግም” ያሉት አፈ-ጉባኤው ታገሰ ጫፉ፣ “ይኽ ሕግ ብዙ ተለፍቶበታል እና መጽደቁ ተገቢ ነው”ም ሲሉ ተደምጠዋል።

## አዲሱ ሕግ ምን ይዟል?

የኢትዮጵያ አዲሱ የፈዴራል የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ዋና ዋና ይዘቶቹ እና ለውጦቹን እንደሚከተለው አጠር አድርገን ልናያቸው ይቻለናል፤

### ሀ፦ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ መዋሃድ፤

ቀደም ሲል የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና የማስረጃ ሕግ ተለያይተው (የማስረጃ ሕጉም በረቂቅ ደረጃ ብቻ ለረጅም ጊዜ መቆየቱን ልብ ይሏል) የነበረ ቢሆንም፣ አዲሱ ሕግ ግን ኹለቱንም በአንድ ላይ አጣምሮ ይዟል። ይኽ መሆኑ

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ግልጽነትና ቅልጥፍናን ይፈጥራል የሚል ዕምነትንም አሳድሯል።

## ለ፦ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ እና የሕግ የበላይነት፤

ዐዋጁ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት እና ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች የተደነገጉ የሰብዓዊ መብቶችን በተግባር ለመተርጎም የተነደፈ ሲሆን፣ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ከዋሉበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መጨረሻው የፍርድ ሂደት ድረስ ያላቸውን መብቶች በዝርዝር በማስቀመጥ፣ የሕግ አስከባሪ አካላት ሥልጣናቸውን ያለአግባብ እንዳይጠቀሙ ገደብ ይጥላል። በተለይም በምርመራ ወቅት የሚፈጸሙ ኢ-ሰብዓዊ አያያዞችን ለመከላከል እና በግዴታ የተገኘ ቃል በማስረጃነት እንዳይቀርብ የሚያደርጉ ድንጋጌዎች የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና የዜጎችን ክብር ለመጠበቅ ዋነኛ ዋስትናዎች ከመሆናቸው አኳያ፣ ለውጡ አሌ የሚባል አይደለም።

## ሐ፦ የዲጂታል ማስረጃዎች ዕውቅና፤

አዲሱ ሕግ የቴክኖሎጂ ለውጥን ያገናዘበ ሲሆን፣ የዲጂታል ወይም የኤሌክትሮኒክስ ማስረጃዎችን (ለምሳሌ፣ የቪዲዮ ምስሎች፣ የድምፅ ቅጂዎች፣ የኮምፒውተር መረጃዎች፣ የማኅበራዊ ሚዲያ መልዕክቶች) እንደ ትክክለኛ ማስረጃ እንዲቀበሉ ሕጋዊ መሠረት ሰጥቷል። የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለምርመራ የመጠቀም አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፖሊስ የኤሌክትሮኒክ መረጃዎች እንዲቆዩ ትዕዛዝ መስጠት የሚችለው ለአንድ ወር ብቻ እንዲሆንም ተደንግጓል። ይኽ የጊዜ ገደብ መረጃዎች ያለአግባብ በመንግሥት እጅ እንዳይቆዩ እና የግለሰቦች የዲጂታል ግላዊነት መብት እንዳይጣስ ዋስትና ይሰጣል። ከዚኹ ጋር በተያያዘ፣ እንደ ስልክ ጠለፋ እና የድብቅ ክትትል ያሉ ዘመናዊ የምርመራ ዘዴዎች በምን ዓይነት ጥብቅ የሕግ ማዕቀፍ እና የፍርድ ቤት ፈቃድ መከናወን እንዳለባቸውም ተደንግጓል።

## መ፦ የዐቃቤ ሕግ ሥልጣን እና ክስ መመስረት፤

በዚኽ አዲሱ ሕግ የተካተተው አንዱ አዲስ ሥነ-ሥርዓት የክስ ድርድር ሲሆን፤ ደንቡም፣ አንድ ተጠርጣሪ ጥፋተኛነቱን አምኖ ከዐቃቤ ሕግ ጋር በመደራደር ቅጣቱ እንዲቀልለት ወይም ክሱ እንዲቋረጥ የሚያስችል ሥርዓት ነው። ይኽም የፍርድ ቤቶችን የሥራ ጫና ከመቀነሱ ባለፈ፣ ንጹሐንን ለግዳጅ የእምነት ቃል እንዳያጋልጥ፣ ዳኛው ተከሳሹን ለብቻው አነጋግሮ ድርድሩ በፈቃደኝነት መደረጉን የማረጋገጥ ግዴታ ተጥሎበታል። በተጨማሪም፣ ለከባድ ወንጀለኞች የሚደረግ የቅጣት ቅናሽ የሕዝብን ጥቅም በማይጎዳ መልኩ እንዲሆን በፍርድ ቤት ቁጥጥር እንዲደረግበት ተደርጓል። ከዚኹ ጋር በተሳሰረ፣ ዐቃቤ ሕግ ክስ ለማንሳት የሚችልባቸውን ምክንያቶች እና ቅድመ-ኹኔታዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል። ቀደም ሲል ዐቃቤ ሕግ 'በሕዝብ ጥቅም ስም' ክስን የማንሳት ሰፊ እና ያልተገደበ ሥልጣን እንደነበረው ይታወሳል። ይኹን እንጂ አዲሱ ማሻሻያ ይኽ ሥልጣን በዝርዝር መመሪያ እንዲገዛ እና የሚሰጠው ምክንያትም ለፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲመረመር ተደንግጓል። ይኽ ለውጥ የአሥተዳደራዊ ውሳኔዎችን

ግልጽነት ከማረጋገጡም በላይ፣ ሥልጣንን ያለአግባብ የመጠቀም ዕድልን በእጅጉ ይቀንሳል ተብሎ ይታመናል።

### ሠ፦የምሥክሮች እና የጠቋሚዎች ጥበቃ፤

በከባድ ወንጀሎች ላይ መረጃ የሚሰጡ ጥቆማ ሰጪዎች እና ምሥክሮች ከበቀል ወይም ከጥቃት እንዲጠበቁ የሚያስችል የሕግ ከለላም በአዲሱ ሕግ ውስጥ ተካቷል፤ ይኽም በብዙ የሕግ አዋቂዎች ዘንድ ሙገሳ ያገኘ አንቀጽ መሆኑ ተስተውሏል።

### ረ፦ የፍርድ ቤት ሥነ-ሥርዓት ቅልጥፍና፤

የፍርድ ቤት ሥነ-ሥርዓት ቅልጥፍና ለማሳለጥ በቅድመ-ችሎት ስብሰባ ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ግልጽ የሆኑ ነጥቦችን ለመለየት እና ሂደቱን ለማፋጠን የሚረዱ አሠራሮችንም አዲሱ ሕግ አስተዋውቋል። ከዚኽ ባለፈም፣ የምርመራ ጊዜ ቀጠሮ አሰጣጥ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ፣ ተጠርጣሪዎች ያለ ፍርድ ለረጅም ጊዜ እንዳይታሰሩ የሚረዱ ድንጋጌዎችንም ይዟል።

### ሰ፦ ባህላዊ ሥርዓታት እና የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ፤

በዚኽ አዲሱ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት መንገዶች ከዘመናዊው የሰብዓዊ መብት መርሆዎች ጋር እንዲጣጣሙም ተደርጓል። በተለይም በሴቶች እና በሕፃናት ላይ በደል እንዳይደርስ፣ የማኅበረሰብ ውሳኔዎች በፍርድ ቤት መጽደቅ እንዳለባቸው እና ሂደቱም በሠላሳ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ መደረጉ በበጎ ለውጥነት ተነስቷል።

## ሦሥት ነጥቦችን በወፍ በረር...

በዚኽ መልኩ አጠር አድርገን ልናያቸው የሞከርናቸውን ለውጦች የያዘውን አዲሱን ሕግ አስመልክቶ ዋንኞች ባልናቸው ሦሥት የሕጉ ድንጋጌዎች ላይ ደግሞ ጥቂት ነጥቦችን በማሳያነት እናንሳ፤ እነዚኽም፣ ዋስትና፣ የጥፋተኝነት ድርድር እና የማስረጃ ሕግ የተሰኙት የሕጉ አዲስ ሥነ-ሥርዓቶች ናቸው።

### ሀ፦ ዋስትና

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 19/6 በግልጽ እንደተደነገገው፣ የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው። ይኽ መብት ሕገ-መንግሥታዊ ሲሆን፣ የተያዙ ወይም የተከሰሱ ሰዎችን መብት ከማስከበር አኳያ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉትም ግልጽ ነው። የመጀመሪያ ጠቀሜታው ሌሎች ሕገ-መንግሥታዊ መብቶችን ማስከበር መቻሉ እና በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሰዎች ሊታሰሩ አይገባም ከሚለው የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የተቆራኘ መሆኑ ነው። የግለሰቦች ነፃነት እንዳይሸረሸር እና ከፍርድ በፊት ያለአግባብ እንዳይታሰሩ በዋስ የመፈታት መብታቸውንም ያስጠብቃል፡፡ አዲሱ ሕግ የዋስትና መብትን እንደ መሠረታዊ መብት፣ ዋስትና መከልከልን ደግሞ እንደ

ልዩ ሁኔታ ይመለከተዋል። ሕጉ ግልጽ የሆኑ የዋስትና ዓይነቶችንም አስቀምጧል፤ እነሱም፤ በግል ማረጋገጫ፣ በሰው ዋስትና፣ በንብረት ዋስትና ወይም በገንዘብ ማስያዝ የሚሉት ናቸው፤ ሆኖም ተጠርጣሪው ዋስትና ቢፈቀድለት ይጠፋል ወይም ማስረጃ ያጠፋል ወይም ተጨማሪ ወንጀል ይፈጽማል ተብሎ ሲታመን ዋስትና ሊከለከል ይችላል። እንዲሁም የቅጣቱ መጠን ከባድ በሆነባቸው (ለምሳሌ በሞት ወይም በዕድሜ ልክ እስራት በሚያስቀጡ) ወንጀሎች ላይ ገደብ ሊኖር ይችላል። ፍርድ ቤቱ ዋስትና ሲፈቅድ ተጠርጣሪው ከአገር እንዳይወጣ ፓስፖርት እንዲያስረክብ፣ የተወሰኑ ቦታዎች ላይ እንዳይገኝ ወይም በየጊዜው ፖሊስ ጣቢያ ቀርቦ እንዲፈርም ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል። ዋስትና የተከለከለ ተጠርጣሪ ወይም ዋስትና የተፈቀደለትን ተቃውሞ ያለው ዐቃቤ ሕግ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማለት መብቱም በግልጽ ተቀምጧል።

የዚኽ መሰሉ ድንጋጌ ዋንኛ ጠቀሜታ፣ በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው በዋስ ሲለቀቅ ከተከሰሰበት ክስ 'ራሱን ለመከላከል የሚያስችለውን ማስረጃ ለማሰባሰብ እና ሌሎች ዝግጅቶችን ለማድረግ የተሻለ ነፃነት ማግኘቱ ነው። በዚህም ሂደት የፍትሕ አካላት እውነትን ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት ከማገዙ ባለፈ፣ የተያዘን ሰው በዋስ መልቀቅ በማረሚያ ቤት ያለውን የእስረኞች መጨናነቅ በመቀነስም አስተዋጽዖ እንደሚኖረውም ማስታወስ ያሻል። በወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩትን ሰዎች በሕግ አግባብ በዋስ መልቀቅ፣ ከፍርድ ሂደት በኋላ በነፃ ሊለቀቁ የሚችሉ ሰዎች በሞራላቸው እና በቁሳዊ ሀብታቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በመቀነስ የዜጎችን ሰብዓዊ ክብር እና ቁሳዊ ጥቅሞችን ለመጠበቅም አንዱ ዘዴ ነውና።

ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የፌዴሬሽኑ ሕገ-መንግሥት የዋስትና መብት ፍፁም እንዳልሆነም፣ በአንቀጽ 19/6 ከተቀመጠው ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። በዚህም መሠረት በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄዎችን ላለመቀበል ይችላል። እነዚህ ሁኔታዎችም፣ የወንጀል ዓይነቶች(ለምሳሌ የሽብርተኝነት ወንጀል)ን፣ የወንጀል ዓይነት እና የቅጣት መጠን (ለምሳሌ የሙስና ወንጀል ሆኖ ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ)ን፣ የቅጣቱ ጣራ (ለምሳሌ በሞት የሚያስቀጣ ከሆነ)ን፣ የተጎጂዎች ዓይነት (ለምሳሌ ሕፃናት እና ሴቶች ከሆኑ)ን የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

## ለ፦ የጥፋተኝነት ድርድር

አዲሱ ሕግ ከያዛቸው አዲስ ስርዓቶች መካከል አንዱ የጥፋተኝነት ድርድር የሚለው ሥርዓት ነው። ይኽም፣ አንድ ተጠርጣሪ ጥፋተኛነቱን አምኖ ከዐቃቤ ሕግ ጋር በመደራደር ቅጣቱ እንዲቀልለት ወይም ክሱ እንዲቋረጥ የሚያስችል ሥርዓት ነው። የጥፋተኝነት ድርድር በኢትዮጵያ የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ አዲስ ሲሆን፣ ዓላማውም ጊዜን እና ወጪን ለመቆጠብ እንዲሁም የፍርድ ቤቶችን ጫና ለመቀነስ ነው ተብሏል። ክስ ከመመሥረቱ በፊት ወይም ክስ ከተመሠረተ በኋላ ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠርጣሪው ጥፋተኛነቱን አምኖ ከዐቃቤ ሕግ ጋር ሊደራደር ይችላል። በ'ርግጥ ብዙ ሰዎች ይኽ አሰራር

ምንም እንኳ በውጪ ሀገር የተለመደ ቢሆንም እንደኛ ባሉ ሀገራት ለሙስና በር ከፋች ከመሆኑም በላይ ፖሊስ ተከሳሾች ላይ አላስፈላጊ ጫና እንዲፈጥር ሊያደርግ ይችላል ሲሉ ስጋታቸውን ይገልጻሉ፡፡

የጥፋተኛነት ድርድር ዓይነቶች ኹለት ሲሆኑ፣ ከባድ የሆነውን ክስ ወደ ቀለል ያለ የወንጀል ዓይነት በመቀየር መደራደር እና በክሱ ላይ ተስማምቶ ቅጣቱ እንዲቀልለት መደራደር ናቸው። ይሁንና ድርድሩ የተደረገው በፈቃደኝነት መሆኑን፣ ተከሳሹ መብቶቹን መረዳቱን እና ድርድሩ የሕዝብን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማረጋገጥ ይኖርበታል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ ፍርድ ቤቱ ድርድሩን ውድቅ የማድረግ ሥልጣን አለው። ዐቃቤ ሕግ የክስ ድርድር ሲያደርግ የወንጀል ተጎጂዎችን ፍላጎት እና ስሜት ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበትም ሕጉ ይደነግጋል። ተጎጂው ካሳ የሚያገኝበት መንገድም በድርድሩ ውስጥ ሊካተት ከመቻሉ ባለፈ፣ ተከሳሹ የቅጣት ቅናሽ ያገኛል፤ መንግስት ለምስክሮች እና ለረጅም ክርክር የሚያወጣውን ወጪ ይቆጥባል፤ ተጎጂዎች ደግሞ የፍርድ ሂደቱን ሳይጠብቁ ካሳ ወይም ይቅርታ ሊያገኙ የሚችሉበትን ኹኔታ ይፈጥራል።

## ሐ፦ የማስረጃ ሕግ

የማስረጃ ሕግ ለፍርድ የሚሆነውን ማስረጃ ለይቶ የሚያሳይ ወይም በፍርድ ሥራ መካሄድ የፍሬ ነገር ጥያቄን ለመወሰን መገልገያ የሆነውን ዘዴ የሚያመለክት ደንብ ነው። ለአንድ ፍርድ ቤት የቀረበ ማስረጃ የሚያስፈልጋቸዉ በጭብጥ የሚያዙ ፍሬ ነገሮችን እና እነዚህን ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት የሚቀርቡት ፍሬ ነገሮችን እና አግባብነት እና ተገቢነት ያላቸው መሆናቸውን የሚወስን ነው፡፡ በግዙፍ ነገር፣ በሠነድ፣ በቃል፣ በዳኞች ግንዛቤ ወይም በተከራካሪዎች እምነት አማካኝነት የሚቀርበውን የማስረጃ ዓይነት፣ እንዲሁም አከራካሪዉ ጉዳይ እውነት መሆኑን እና አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ እንዲያምን የሚደረግበትን መንገድ የሚገዛም ነው። በመሆኑም አዲሱ ሕግ እነዚህን በሙሉ ከመዘርዘርም ባሻገር አንድ ማስረጃ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ተገቢ የሚሆነው መቼ እንደሆነ እና ውድቅ የሚሆነው መቼ መሆኑን በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ለምሳሌ ፖሊስ በድብደባ ከተከሳሹ ያገኘው የእምነት ቃል ወይም ፍርድ ቤቱን ሳያስፈቅድ ስልክ በመጥለፍ (ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ) ያገኘው ማስረጃ ተቀባይነት የለውም።

በተጨማሪም፣ ከላይ እንደጠቀስነው አዲሱ ሕግ የዲጂታል ወይም የኤሌክትሮኒክስ ማስረጃዎችን እንደ ትክክለኛ ማስረጃ እንዲቀርቡ ሕጋዊ መሠረት ሰጥቷል። ሆኖም እንደ ስልክ ጠለፋ እና የድብቅ ክትትል ያሉ ዘመናዊ የምርመራ ዘዴዎች በምን ዓይነት ጥብቅ የሕግ ማዕቀፍ እና የፍርድ ቤት ፈቃድ መከናወን እንዳለባቸውም ደንግጓል። ምክንያቱም ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት ከአገሪቷ የሕገ-መንግሥት መርሆዎች መካከል አንዱ መሆኑን ያስታውሷል። አዲሱ ሕግ ካስተዋወቀው መሰረታዊ የማስረጃ መርሆዎች አንዱ የማረጋገጫ ደረጃ ነው። ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው ዐቃቤ ሕግ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል መፈፀሙን በማስረጃ ካረጋገጠ ብቻ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ የተከሳሹ ጥፋተኝነት የሚረጋገጥበት ደረጃ ከፍ እና ጠበቅ ያለ መሆን አለበት። አዲሱ ሕግ ዐቃቤ ሕግ አንድን ተከሳሽ ጥፋተኛ ለማስባል

‘ከበቂ ጥርጣሬ በላይ’ ክሱን ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት እንዳለበት በግልጽ አስቀምጧል። ይኽ መርህ በሕግ ደረጃ መደንገጉ የተከሰሾችን ሕገ-መንግሥታዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ መብት ከማስጠበቅ አኳያ ትልቅ እመርታ ሆኖም ተቆጥሯል። በ‘ርግጥ ፖሊስ እና ዐቃቤ ሕግ ባለባቸው የአቅም ውስንነት በዚህ ደረጃ የምርመራ እና የክስ ሂደቱን ማከናወን መቻላቸው አጠያያቂ ቢሆንም፣ አቅም ያጥረኛል በሚል ከዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት መርሆዎች መጉደል ተገቢነትም፣ የሚጠበቅም አይሆንም።

## እንደ መውጪያ

የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ የኅብረተሰቡን እና የመንግሥትን ደኅንነት እና ሰላም ሲያስጠብቅ ኹለት ተገዳዳሪ ጥቅሞችን በማመዛዘን መሆን ይኖርበታል። በአንድ በኩል የመንግሥት እና የኅብረተሰብን ሰላም እና ደኅንነት ለማስጠበቅ የወንጀል ሕግ የሚተላለፉ ግለሰቦችን ውጤታማ፣ ፍትሓዊ፣ ቀልጣፋ እና አስተማማኝ በሆነ ሂደት በሕግ ፊት አቅርቦ አራሚ እና አስተማሪ የሆነ ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ፤ በሌላ በኩል ቅጣቱ በንፁሐን ላይ ሳይሆን በአጥፊዎች ላይ ብቻ እንዲፈፀም ብርቱ የጥንቃቄ እርምጃዎች ማስቀመጥ ይጠበቅበታል። ቅጣቱ በአጥፊዎች ላይ ብቻ የሚፈፀምበት ሂደትም ቢሆን የአጥፊውን ሰብዓዊ ክብር እና ማንነት በማይጎዳ ሁኔታ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥነ-ሥርዓት ማስቀመጥም ይጠበቅበታል። ከኹሉም በላይ ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት ለወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ መርህ የሆነውን ያህል፣ ለማስረጃ ሕግም መርህ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ሌላው ጉዳይ ይኽ መርህ ትርጉም እና ተፈፃሚነት የሚያገኘው አገራት በሚከተሉት የሕግ ሥርዓት ዓይነት ላይ በመመሥረት ነው። ምንም እንኳ በእኛ አገር ሕግ ውስጥ በግልፅ ያልተፃፈ ቢሆንም የአገራችን ፍርድ ቤቶች ‘ከበቂ ጥርጣሬ በላይ’ የሚለውን የጥፋተኝነት ማረጋገጫ ደረጃ የሚጠቀሙበት መሆኑ ይታወቃል። ከጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት መርህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ፣ ዐቃቤ ሕግ የተጠርጣሪውን ጥፋተኝነት ሲያረጋግጥ ኹሉንም የወንጀሉን ፍሬ ነገሮች በተቀመጠው የማረጋገጫ ደረጃ መሠረት ማረጋገጥ ይጠበቅበታል የሚለው ነው።

በአጠቃላይ፣ አዲሱ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ‘ንጹሕ ሆኖ የመገመት’ን መርህ ወደ ተግባር የሚቀይር፣ የሕዝብን ሰላም ከግለሰቦች ሰብዓዊ መብት ጋር የሚያመጣጥን ሰነድ ነው ማለት ይቻል ይመስለናል። ሕጉ፣ እንደተባለው ለሥድስት ዓመታት በጥንቃቄ የታየ ቢሆንም፣ የአተገባበሩ ስኬት የሚለካው በፖሊስ፣ በዐቃቤ ሕግ እና በፍርድ ቤቶች ነጻነት እና ተከታታይነት ያለው ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ላይ መሆኑንም መዘንጋት አያስፈልግም። ከዚኽ አኳያም ብሪጅ፣ ፖሊስ እና ዐቃቤ ሕግ ‘ከበቂ ጥርጣሬ በላይ’ ለማስረዳት የሚያስችል የፎረንሲክ እና የምርመራ አቅም ሊገነባላቸው ይገባል ብላ ታምናለች። ከላይ ያነሳውነውን፣ የአዲሱን ሕግ አንቀጽ 25(3) ተንተርሶ የተደመጡት ቅሬታዎችም በፖለቲካ ገጾች በኩል ሳይሆን በሕግ ትርጓሜ ብቻ እንዲፈቱ ብርቱ ክትትል ያስፈልጋል እንላለን። ዜጎችም ስለ አዲሱ የዲጂታል መብታቶቻቸው እና ስለ ዋስትና መብታቸው በቂ የግንዛቤ

ትምህርት የሚያገኙበትን መንገድ ዋል አደር ሳይባል ሊበጅ እንደሚገባም፣ ተቋማችን ማስታወስ ትሻለች።

## 9. የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ የኢትዮጵያ ሴቶች የእንደራሴነት መንገድ፣ ከማርች ስምንት ማዶ

ወሩ መጋቢት እንደመሆኑ፣ ኢትዮጵያም 50ኛውን የሴቶች ቀን ደርበብ ባለ ሥርዓት አስባው ውላለች። ሴት እንደራሴዎቿም በ'የዓመቱ መጋቢት 4 ቀን የሚከበረውን ይኸንኑ ዓለም ዓቀፉን የሴቶች ቀን አክብረው ውለዋል። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት አመራሮች እና ሠራተኞች በተገኙበት ዓለም ዓቀፉ የሴቶች ቀን፣ "የሴቶች ድምጽ ለእኩልነት እና ለበለጸገች ኢትዮጵያ" በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ዝግጅቶች መከበሩን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷል። ይኸ ኹነትም፣ ስለ ኢትዮጵያ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ፣ የእንስት እንደራሴዎቹ ትናትናዎች እና ተግዳሮቶች እንዲኹም ዛሬዎቻቸውን አጠር አድርጎ ለመዳሰስ የብሪጅ የመጋቢት ዳሰሳ ርዕሰ-ጉዳይ ገፊ ምክንያት ሆኗል። ከዚኽ አኳያም፣ እነዚኽን መሠረታዊ ጥያቄዎች በጥቂት ኃልዮታዊ ነጥቦች አስደግፈን እና አሃዛዊ መረጃዎችን እያሰባጠርን ልንመለከታቸው መርጠናል።

### የሴቶቻችን ትናንቶች

በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እንደ እቴጌ ጣይቱ እና ንግሥት ዘውዲቱ ያሉ ብርቱ ሴቶች አንድም በአገረ-መንግሥቱ ላይ በነበራቸው የመሪነት ቦታ፤ አንድም በዓድዋ ጦርነት ወቅት በነበራቸው ሚና ቢታወቁም፣ የሴቶች ተቋማዊ የፖለቲካ ውክልና ግን የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው። በኢትዮጵያ ዘመናዊ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ታሪክ፣ በ1923 ዓ.ም. በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሲጀመር የሴቶች ውክልና እጅግ አነስተኛ ነበር። በወቅቱ በሕዝባዊ የፖለቲካ ተዋስዖ ውስጥ የሚታዩት ጥቂት የባላባቶች፣ የመኳንንት እና የጦር መኮንኖች ሚስቶች ብቻ ነበሩ።

ለሴቶች የመምረጥ መብት የሕግ መሠረት የሆነው የ1948ቱ የተሻሻለው ሕገ-መንግሥት ቢሆንም፣ የመጀመሪያዋ ሴት እንደራሴ የተመረጠችው በ1949 ዓ.ም. ነበር። በዚኽም ምክንያት ሴቶች ከከፍተኛ የአመራር ቦታዎች ተገልለው የቆዩ ሲሆን፣ በ1957 እና በ1961 ዓ.ም. በነበሩት ምርጫዎች የሴቶች ቁጥር በተከታታይ 2 እና 5 ብቻ ነበር። ምንም እንኳ በወቅቱ የሴቶች ንቅናቄዎች ቢጀመሩም ቅሉ፣ ንቅናቄዎቹ ወደ ጠንካራ የፖለቲካ ተጽዕኖ አምጪነት የመለወጥ አቅም አልነበራቸውም።

ኢትዮጵያውያን ሴቶች ዋጋ ባለው መንገድ ያሳዩት የፖለቲከኝነት ተላምዶት፣ እንደሌሎች የአገሪቱ ዘመናዊ የፖለቲካ ጅማሮዎች ኹሉ ዘመኑን ከ1960ዎቹ መጀመሪያ ይዋረሳል። ፖለቲካዊ አደባባዩ ላይ መቆም ለወንዶች ብቻ የተፈቀደ አድርጎ በሚያስብ ማኅበረሰባዊ ሥርዓት ውስጥ የእንስቶቹ ወደፊት መምጣት፣ የተማሪዎች ንቅናቄ አንደኛው ግዙፍ አስተዋጽዖ እንደሆነ የንቅናቄውን ዘመን የሚተርኩ ፀሐፊዎች ሁሉ ይስማማሉ።

ጸሐፍቱ እንደሚያመለክቱት፣ ራሱን በዋናነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያጠረው የተማሪዎች ንቅናቄ፣ ለሴቶቹ የ'ራሳቸውን ድምፅ የሚያሰሙበት ከወንዶች ተጽዕኖ የፀዱ ተቋማት እንዲኖራቸው ባይፈቅድላቸውም፣ ዘግይተው በተመሰረቱት ፓርቲዎች በኩል ፆታን ማዕከል የሚያደርጉ

ፖለቲካዊ ፍላጎቶቻቸውን ለመወከል ተሞክሯል። ጥናቶቹ እንደሚያትቱት፣ መኢሶን እና ኢሕአፓ የኢትዮጵያውያን ሴቶችን ጥያቄ፣ የመደብ እና የፆታ መንታ መልክ አድርገው አቅርበውታል። ከውስጠ-ፓርቲ መዋቅራቸው እና ከርዕዮተ-ዓለም ዝማሜያቸው አንፃር የፆታ-ፖለቲካውን በዚኽ መንገድ ሊበይኑት ቢሞክሩም፣ የፓርቲዎቹ ከፖለቲካው መድረክ በጭካኔ መወገድ በኋላ የሴቶች መነቃቃትም በከፍተኛ ኹኔታ ተቀዛቀዘ።

ደርግ ሥልጣን ሲይዝ የሴት እንደራሴዎቹ ቁጥር ወደ 4 ዝቅ ቢልም፣ ሴቶቹ ግን በሴቶች ጥያቄ ዙሪያ በተማሪዎች ንቅናቄ እና በተከታታይ አደባባይ ሰልፎቹ ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረጋቸው በስፋት ተመዝግቧል። የሴቶች የተደራጀ የፖለቲካ ተሳትፎ መነሻው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ሲሆን፣ በወቅቱ ስለ ሴቶች ጥያቄ የሚደረጉ ክርክሮች ለንቃተ-ህሊና ዕድገቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበራቸው።

ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በ1967 ዓ.ም. የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴን በማቋቋም ሴቶች ከቤት ውስጥ ሥራ ወጥተው በይፋ እንዲደራጁ መንገድ ከፍቷል። ሆኖም የሥርዓቱ ርዕዮተ-ዓለም መጀመሪያ ላይ የሴቶችን ችግር እንደ ድርብ ጭቆና (የመደብ እና የጾታ) ቢመለከተውም፣ ከ1970 ዓ.ም. በኋላ ግን "የመደብ ጭቆና ከጾታ ጭቆና ይበልጣል" የሚል አቋም በመያዙ የሴቶች ጥያቄ ለሶሻሊዝም ድል ተገዥ እንዲሆን ተደርጓል። ይኽም የጾታ ጭቆናን ትርጉም ባለው መልኩ ለመለወጥ ለተጀመረው ጾታ ተኮር ትግል እንቅፋት መሆኑ አልቀረም።

በ1967 ዓ.ም. የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ፣ በ1972 ዓ.ም. ደግሞ የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ማኅበር (ኢሴማ) ተመሠረተ። ደርግ በ1972 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ማኅበር (ኢሴማ)ን እስከ ታችኛው የሥልጣን እርከን ድረስ በማዋቀር የሴቶችን ተሳትፎ በቁጥር ለማሳደግ ጥረት ማድረጉም ይነሳለታል። ያም ሆኖ የማኅበሩ አመራሮች የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) አባላት ስለነበሩ፣ ሴቶች የራሳቸውን አጀንዳ የመቅረጽ ሥልጣን አልነበራቸውምና ማኅበራቱ የሥርዓቱ ርዕዮተ-ዓለም ማጥመቂያ እንጂ ሴቶችን በፖለቲካው እውነተኛ ተሳታፊ የሚያደርጉ አልነበሩም።

በ1979 ዓ.ም. የጸደቀው የኢሕዲሪ ሕገ-መንግሥት የሴቶችን የእኩልነት መብት በግልጽ እውቅና የሰጠ የመጀመሪያው ሰነድ ቢሆንም፣ በወቅቱ በነበረው የ'ርስ በ'ርስ ጦርነት ምክንያት በተግባር ሳይውል መቅረቱ ይታወሳል። እናም ደርግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ የአብዮታዊያን ኢትዮጵያውያን ሴቶች ማኅበርን መሰል የራሱን ክንፍ በማቋቋም ሶሻሊስት እንስታዊነትን ለመተርጎም እንደሞከረ ቢያምንም፣ ጉዳዩን ያጠኑ በዚኽ አይስማሙም። እኒኽ መሰሎቹ ጸሓፍት፣ ደርግ በአኢሴማ በኩል ያደራጃቸው ሴቶች፣ ለሥርዓቱ ወታደሮች ምግብ እንዲያበስሉ ከማድረግ ባለፈ የ'ነርሱን ፍላጎት ለመፍታት አንዳች ጥረት ባለማድረጉ ይወቅሱታል።

በአንጻራዊነት ሕወሓት በሜዳ ትግሉ ዘመን የተሻሉ ሙከራዎችን አድርጓል ተብሎ ይጠቀስለታል። የወቅቱን የትግራይ ሴቶች ተሳትፎ ታሪካዊ ሲሉ የሚጠሩ የዘመኑ ዘጋቢዎች፣ ግንባሩ ያደረጋቸው በዘመኑ ማኅበረሰብ ውስጥ

ስር ሰዶ የነበረውን ጾታዊ ኢ-እኩልነት የሚያስወግዱ ድርጊቶችን ይጠቅሳሉ። የጋብቻ ዕድሜን ከመገደብ አንስቶ በሞከራቸው የመሬት ማሻሻያ ፕሮግራሞቹም፣ የትግራይ ሴቶችን ከቀደመው ጊዜ የተሻለ አቅም እንዲያገኙ ማስቻሉ ይነሳለታል። ያም ቢሆን ግና፣ ብዙዎች እንደሚያምኑት ከደርግ ውድቀት ወዲኽ ፓርቲው ዋጋ የከፈሉለትን ሴቶች ወደ ጎን አሽቀንጥሯቸዋል።

በ1983 ዓ.ም. የደርግ ውድቀትን ተከትሎ ኢሕአዴግ በአገር ዓቀፍ ደረጃ ያለውን የጾታ ኢ-እኩልነትን ለመፍታት ጥረት ያደረገ ሲሆን፣ የ1987ቱ ሕገ-መንግሥት የሴቶችን መብት በግልጽ በማረጋገጥ፣ ሴቶች በፖለቲካው ንቁ እንዲሆኑ ልዩ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ደንግጓል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ሴቶች በኹሉም የሥልጣን እርከኖች ላይ በተገቢው ሁኔታ አልተወከሉም ነበር የሚለው፣ ቢያንስ እስከ 2010 ለነበረው የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሥርዓት ኹነኛ መደምደሚያ ነው።

ከ2010 ዓ.ም. የፖለቲካ ሽግግር በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ በሴቶች የፖለቲካ ውክልና ረገድ አዳዲስ እርምጃዎችን ወስደዋል። ጥቅምት 18 ቀን 2018፣ 20 አባላት ያሉት እና ግማሹ ሴቶች የሆኑበት የጾታ እኩልነት የተጠበቀበት ካቢኔ አቋቁመው እንደነበርም ይታወሳል። ይኽም ቀደም ሲል ከነበሩት 28 ሚኒስትሮች መካከል 4ቱ ብቻ ሴቶች ከነበሩበት ኹኔታ የተቀየረ ትልቅ እርምጃ ተደርጎ ሲወደስ ተስተውሏል። ኢትዮጵያም በዚኽ እርምጃዋ እንደ ሩዋንዳ ያሉ አገራትን ተሞክሮ በመከተል ዓለም ዓቀፍ ሙገሳን አግኝታበት ነበር። በዚኽ አዲስ አደረጃጀት ሴቶች እንደ መከላከያ፣ ሰላም፣ ንግድ፣ ሳይንስ እና ፋይናንስ ያሉ ወሳኝ የሥልጣን ቦታዎችን መያዝ ጀምረዋል።

ኢንጂነር አይሻ መሐመድ የአገሪቱ የመጀመሪያዋ ሴት መከላከያ ሚኒስትር፣ ሙፈሪያት ካሚል የመጀመሪያዋ ሴት የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ እና ኋላ የፌደራል መንግሥቱ ሚኒስትር (በሰላም ሚኒስትርነታቸው)፣ ወይዘሮ መዓዛ አሸናፊ የመጀመሪያዋ ሴት የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት፣ ብርቱካን ሚደቅሳ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ፣ እንዲኹም ሳህለወርቅ ዘውዴ የአገሪቱ የመጀመሪያዋ ሴት ርዕሰ-ብሔር በመሆን በኢትዮጵያ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ከፍተዋል።

በእርግጥም በሥራ አሥፈጻሚው ዘርፍ የታየው የሴቶች ውክልና ዕድገት እጅግ ከፍተኛው መሆኑ አሌ አይባልም። በዚኽም፣ በ2009 ከነበረው 10 በመቶ የሴት ሚኒስትሮች ቁጥር፣ በኹለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ወደ 47.6 በመቶ ከፍ ብሏል። ይኽ ለውጥ ኢትዮጵያ በጾታ እኩልነት ረገድ የደረሰችበትን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የሚያረጋግጥ ነው ሲያስብልም ሰንብቷል፤ ሰንብቷል የሚያሰኘውም፣ የተወሰኑት ሴት ሹመኞች በተለያዩ መነሾች ከሥልጣናቸው መነሳታቸው፣ ውዳሴው ላይ ጥላ በማጥላቱ ይመስላል።

## እንዴት ይሳተፉ?

የሴቶቻችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ በዚኽ መልኩ በወፍ በረር እንዳየነው፣ እጅጉን ከተባዕቱ ወገን ዝቅ ያለ መሆኑ፣ ዛሬም እንስቶቹ እንዴት በፖለቲካው ውስጥ ይሳተፉ የሚለውን ጥያቄ በመለስ ቀለስ የሚያስነሳ ርዕሰ-ጉዳይ ነው። ከዚኽ

እንደርም፣ ጥቂት ኃልዮታዊ ነጥቦችን ማንሳት ረብ ሳይኖረው አይቀርም።

ሴቶች በፖለቲካዊ ሥርዓት ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ አስመልክቶ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ኃልዮቶች ቢኖሩም፤ በጉዳዩ ተከታታዮች በቀዳሚነት የሚቀነቀኑት ሦሥት ሙግቶች ናቸው። የመጀመሪያው ማጠንጠኛ፤ ሴቶቹ ራሳቸው በፖለቲካ ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸው ጥልቅ ፍላጎት ላይ ይንተራሳል። ይኽን ፍላጎት የመጀመሪያው ደጃፍ ሲሉ የሚጠሩት አጥኚዎቹ፣ ሴቶቹ የተሳታፊነት ፍላጎት ቢኖራቸውም ይኽ ብቻውን ብዙም እንደማያስኬድ ይናገራሉ። በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ነባራዊ አውዶች የተመቻቹ መሆን፣ ይኽን የሴቶቹን ፈቃድ ለመተግበር የግድ አስፈላጊ የሚባሉ ጉዳዮች ናቸው።

አጥኚዎቹ እንደሚያነሱት ኹኔታዎችን የተሻለ የሚያደርጋቸው መልካም ሊባል የሚችል ፖለቲካዊ ሥርዓት ህልው መሆኑ እና ወደ ፖለቲካው የሚመጡ ሴቶች ወደ አደባባይ ለመቅረብ የሚያስችላቸው የገንዘብም ሆነ ቁሳዊ ምንጮች መኖር ነው። እነኚህን ኹነቶች የተሳለጡ ሊያደርጓቸው የሚችሏቸው በዋናነት ማጠንጠኛቸውን በሴቶች ላይ ያደረጉ ንቅናቄዎች አልያም ተቋማት መብዛት ሲሆን፤ ለመሳተፍ ፈቃደኛ የሆኑት ሴቶች፤ 'ራሳቸውን በፖለቲከኝነት ለማውጣት የሚያስችሉ ቁሳዊም ሆነ የገንዘብ-ነክ ነገሮች መሟላት አልፎም የታየ ኢ-ፍትሓዊነትን ለማርገብ ፖለቲካዊ ውክልና ይገባናል የሚሉ ንቅናቄዎች ጎልተው መውጣት ሴቶችን ወደ ፖለቲካው ይስባል።

ሌላይኛው የሐሳብ ጫፍ፣ የማኅበረሰቡ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ተለዋጮች የሴቶችን ፖለቲካዊ ስኬት አስመልክቶ የሚኖራቸውን ድርሻ ይይዛል። እንደ ሐሳቡ ተሟጋቾች፤ ሴቶች በአንድ አገር ውስጥ የሚኖራቸው የፖለቲካ ተሳትፎ አገሪቷ ውስጥ ባሉት እነዚኽ ጭብጦች ላይ ይወሰናል። የነገሩ ጸሓፍትም ይኽን ጉዳይ በሚገባ ለመረዳት አውዶቹን በሦሥት ዘርፎች ይከፋፍሏቸዋል።

የመጀመሪያው፤ ሴቶች ከፖለቲካው ውጪ በሌሎች ማኅበራዊ ፈርጆች ላይ የሚኖራቸው ስኬት ፖለቲካዊ ተጋብሮነታቸውን እንደሚወስን ጸሐፊዎቹ ይጠቅሳሉ። ከዚኽ እንደርም፣ የሴቶች በትምህርት ስኬታማ መሆን ወደ ፖለቲካው ለመምጣት እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው ሲሉ ጸሐፊዎቹ ይከራከራሉ። ሴቶቹ ጋዜጠኞች፣ የሕግ ትምህርት ባለሙያዎች አልያም የቢዝነስ ሰዎች ከሆኑ ከሌሎች አቻዎቻቸው ይልቅ በፖለቲካው ስኬታማ መሆን ይቻላቸዋል ሲሉም ይሟገታሉ። ለርዕሰ-ጉዳዩ አጥኚዎች የዚህ ምክንያቱ ግልፅ ነው፤ በተጠቀሱት ሙያዎች ስኬታማ መሆን የቻሉ ሴቶች፣ ከእነዚህ ፈርጆች በራስ መተማመንን፣ በሕዝባዊ አደባባዮች የመናገር ድፍረትን እንዲያገኙ እንዲኹም ከአገሪቱ ሕግጋት እና ነባራዊ ፖለቲካዊ ጭብጦች ጋር ጥልቅ ተላምዶት ስለሚኖራቸው ራሳቸውን ወደፖለቲከኝነት ለመቀየር አይቸገሩም።

ኹለተኛው ነጥብ ከላይ ከጠቀስነው ሐሳብ ጋር ይዛመዳል። ይኽም በአገሪቱ ውስጥ እጅግ ጠንካራ ሊባል የሚችል ጾታ-ተኮር ንቅናቄ መኖር ሲሆን፣ የዚኽ ፋይዳም በሥርዓቱ የሚተገበሩትን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊም ሆነ የፖለቲካ አጀንዳዎች በመጫን የሴቶችን ጥያቄ ወደ ሐሳቦቹ

መቀላቀል ያስችላል የሚል ነው። ከጾታዊ የተንሸዋረሩ ዕይታዎች የነጻ ማኅበረሰብ መኖር ለሴቶች የፖለቲካ ተወካይነት መጎልበት የተጠቀሰ የመጨረሻው ነጥብ ሲሆን፣ እንደ ጸሓፍቱ ክርክርም፣ የፖለቲካ ባህሉ በወንዶች ብቻ የማይበየን፣ 'ፖለቲካን መስራት ለሴቶችም እንግዳ ኹነት አይደለም' ብሎ የሚያምን ማኅበረሰብ፣ እንስቶቹን በፖለቲካ ለማጎልበት አይቸገርም።

ሦሥተኛው የጉዳዩ መተንተኛ የሐሳብ ማዕቀፍ በዋናነት የምርጫ ሥርዓትን እና የፆታ ኮታን የሚያቅፈው ፖለቲካዊ ኃተት ነው። ድምጾችን ወደ ወንበር ቁጥር የመቀየሪያ መንገድ ተብሎ በተለምዶ የሚጠራው የምርጫ ሥርዓት፣ አኹን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በሥራ ላይ ካሉት የምርጫ ሥርዓት አማራጮች የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት፣ እንስቶችን ወደ ፖለቲካው ለማቅረብ የተሻለ እንደሆነ ሰፊ ምሁራዊ ዕምነት የተጣለበት የምርጫ ሥርዓት ሆኗል።

በፆታ-ተኮር የፖለቲካ ተዋስዖ ላይ በስፋት የሰሩት እንደሚከራከሩት፤ በተመጣጣኝ የምርጫ ውክልና አካሄድ አንድ የምርጫ ተወዳዳሪ ፓርቲ ለአንድ የምርጫ ወረዳ በዛ ያለቁጥር ያላቸውን አባላቱን በዕጩነት እንዲያቀርብ ስለሚያስችለው፣ ሴቶችን ማዕከል የሚያደርጉ ፖሊሲዎችን ተንተርሶ ድጋፉን ለማስፋት ሴት ዕጩዎችን እንዲያቀርብ ይገፋፋል። እንደሚታመነውም፣ ፓርቲዎች አንድ ዕጩ ብቻ የሚያቀርቡበት አካሄድ ከተጠቀሰው በተጻራሪው ለወንድ ፖለቲከኞች የተመቻቸ ዕድል ስለሚፈጥር የሴቶችን ተሳትፎ ያጎድላል።

በፈርስት-ፓስት-ዘ-ፖስት የምርጫ ሕግ መራጮች እንዲመርጡ የሚገደዱት ለምርጫ ከቀረቡት ፓርቲዎች የመሆን እድሉ ሲሰፋ፤ ከዚኽ በግልባጩ በተመጣጣኝ ውክልና አካሄድ እያንዳንዶቹ ፓርቲዎች ካቀረቧቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ዕጩዎች ውስጥ የማስመረጥ ዕድልን ያገኛሉ። ይኼም ለሴቶች የተሻለ ዐውድ ይፈጥርላቸዋል። ይኽ አውድም፣ የሴቶችን ወደ ጎን መገፋት መግታት የሚቻለው 'ነርሱን ወደ ፖለቲካዊ ተቋማት በማምጣት ነው ለሚሉ የአንስታዊነት የሐሳብ ጫፎች በማኅበረሰቡ ውስጥ መፋፋት ከፍተኛ አስተዋጾዖ ያደርጋል። ከዚኹ ጭብጥ ጋር በተሰናኘ በአጥኚዎቹ የሚነሳው፣ በአንድ ምርጫ ወረዳ ላይ ለተለያዩ የምርጫ ዕርከኖች (ለፌዴራል፤ ለክልል አልያም ለአካባቢ ምክር ቤቶች) በማዕከላዊ መንግሥቱ የሚፈቀደው የወንበር ቁጥር ሲሆን፣ ቁጥሩ እየበዛ ሲመጣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሴቶቻቸውን ወደፊት ለማምጣት ሲደፋፈሩ፤ በግልባጩ የተፈቀዱት ወንበሮች ቁጥር ካነሰ የሴቶቹም የተሳታፊነት ዕድል በዛው ልክ ይሸረሸራል የሚለው የሙግት ሥነ-ሐሳብ ነው።

ሌላይኛው የመከራከሪያ ነጥብ፣ የፖለቲካው ሥርዓት ተለዋጭ ጾታዊ አለመመጣጠንን ለማርገብ በብዙ አገራት የሚተገበረው የኮታ ሥርዓት ነው። በጭብጡ ላይ ያጠኑት ምሁራን የኮታ ሥርዓቱን በሦሥት ይከፍሉታል። የመጀመሪያው ሴቶች ሕግ አውጪ ምክር ቤት ውስጥ የተወሰኑ ለ'ነርሱ ብቻ የተተዉ ወንበሮች እንዲያዙላቸው የሚያስገድድ የሕግ ማዕቀፍ ሲሆን፤ ይኽን እየተገበሩ ያሉትም የኮታ አካሄድን በቅርቡ መጠቀም የጀመሩ አገራት ናቸው።

ኹለተኛው አፈራረጅ፣ በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው የሴቶችን የተሳታፊነት ቁጥር አስመልክቶ የሚኖራቸው የውስጠ-ፓርቲ ደንብ ነው። ይኽ ደንብም፣ ፓርቲዎች ለዕጩነት ከሚያቀርቧቸው አባላት መካከል የተወሰኑት በሴቶች መሞላት እንዳለበት የሚደነግጉበት አግባብ ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩትም፣ በብዙ አገራት ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይኽን አማራጭ ሲጠቀሙ ለዚህ በምክንያትነት የተጠቀሰው፣ የሴቶችን በፖለቲካው ማሳተፍ ግድ የሚሉ የፌዴራል ሕግጋት መኖር ነው።

በመጨረሻ የሚነሳው የኮታ ዓይነት መለዮዎቹን ከቀደሙት ኹለቱ ጋር ያስተሳስራል። ኹሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሴቶች የተወሰኑ ልኬቶችን እንዲያስቀምጡ በሕግ ሲገደዱ እና ፓርቲዎቹም በ'ራሳቸው አቅም ልክ መነሻ የሚሆኑ የድርሻ ማዕቀፎችን ሲያስቀምጡ ይኽን ዓይነት የኮታ አካሄድ ይተገበራል ይላሉ ጸሓፍቱ። እነዚኽን የኮታ የአፈራረጅ መንገዶች በኹለት ጭብጦች መጠቅለል እንደሚቻል የሚናገሩት የነገሩ ፀሐፊዎች፣ ኢ-ፍትሓዊ ምርጫዎች በሚያደርጉ አምባገነን መንግሥታት የጾታ ተኮር ፖለቲካን የድጋፍ ማሰባሰቢያ ለማድረግ ሲያስቡ፣ ሴቶችን በስፋት እና በፍጥነት ወደ ፖለቲካው ለማካተት ይመርጣሉ ይላሉ፤ በሌላ ጫፍ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት በጎለበተባቸው አገራት ያሉ ገዢ ፓርቲዎች የሚመረጡት አካሄድ የእንስቶቹን ዘገምተኛ የተሳታፊነት ሂደት ነው።

## የሴት እንደራሴዎቹ የውክልና ምጣኔ በወፍ በረር

ባለፉት ሠላሳ ዓመታት በኢፌድሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ውስጥ የሴቶች ውክልና ጉልህ ለውጦችን አስተናግዷል። በኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ በ'የምርጫ ዘመኑ በከፍተኛ ኹኔታ እየጨመረ መጥቷል።

በ1987 ዓ.ም. በተካሄደው የመጀመሪያው አገር ዓቀፍ ምርጫ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ውስጥ የነበረው የሴቶች ቁጥር 15 (2.7 በመቶ) ብቻ የነበረ ቢሆንም፤ በኹለተኛው የምርጫ ዘመን ወደ 42 (7.7 በመቶ) አድጓል።

በሦሥተኛው የ1997ቱ ፌደራላዊ ምርጫ ደግሞ ይኽ ቁጥር ከፍ ብሎ ወደ 116 (21.4 በመቶ) ደርሷል። ዕድገቱም ቀጥሎ በ2002ቱ አራተኛው ብሔራዊ ምርጫ 152 (27.8 በመቶ) የደረሰ ሲሆን፣ በ2007 ደግሞ ከጠቅላላው 547 የምክር ቤት ወንበሮች ውስጥ በ210ሩ ምርጫ 38.8 በመቶ፣ እንዲኹም በ2013ቱ 42 በ መቶ ድርሻን በመያዝ ከፍ ያለ ምጣኔን አሳይቷል። ከዚኽ አኳያም፣ ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሴቶች አማካይ ውክልና በ'የምርጫው የ6.6 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ይኹን እንጂ አጠቃላይ የሠላሳ ዓመታት አማካዩን ስንመለከት፣ ሴቶች የያዙት ወንበር 23 በመቶ ብቻ ሲሆን፣ ቀሪው 77 በመቶ በወንዶች የተያዘ መሆኑ የጾታ ስብጥሩ አኹንም ወደ ወንዶች ያዘነበለ መሆኑን በሚገባ ይጠቁማል።

ከእንደራሴነት ባለፈም እንደ አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈ-ጉባኤ ያሉ ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪነት ቦታዎችም የውክልናው መለኪያ መሆናቸውን ልብ ይሏል። ባለፉት የምርጫ ዘመናት ሴቶች በምክትል አፈ-ጉባኤነት ሚና የተሻለ ተሳትፎ የነበራቸው ቢሆንም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ታሪክ ውስጥ ግን እስከ አኹን አንድ ሴት አፈ-ጉባኤ ብቻ መሾሟ፣ ወደፊት የጾታ እኩልነትን በተሟላ እና በዘላቂነት ለማረጋገጥ ተጨማሪ የሕግ እና የመዋቅር ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉ ያመላክታል።

ነገረ-ጉዳያችንን ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ሻገር አድርገን ወደ ፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ስንወስደውም ብዙም የተለየ አሃዛዊ መረጃዎችን አናገኝም። ባለፉት ሠላሳ ዓመታት በኢትዮጵያ በተካሄዱት ሥድስት ተከታታይ አገር ዓቀፍ ምርጫዎች በፌዴሬሽን ምክር ቤት የነበረው የሴቶች ውክልና አዝጋሚ ለውጥ አሳይቷል።

በ1987 ዓ.ም. በተካሄደው የመጀመሪያው አገር ዓቀፍ ምርጫ ከነበሩት 110 የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት መካከል ሴቶቹ 7 (6.7 በመቶ) ብቻ ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 103 ወንበሮች በወንዶች የተያዙ ነበሩ። ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በተለየ ኹኔታ፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ከፍተኛው የሴቶች ውክልና የተመዘገበው በ2007 ዓ.ም. በነበረው አምስተኛው አገር ዓቀፍ ምርጫ ሲሆን፣ ይኽም 50 (32.6 በመቶ) ወንበሮችን የያዙበት ዓመተ-ምርጫ ነበር። ሆኖም ይኽ ቁጥር በ2013 ዓ.ም. በተካሄደው ሥድስተኛው ምርጫ ወደ 43 (30 በመቶ) ዝቅ ብሏል። ለዚኽ መቀነስም በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል ተከስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት የትግራይ ክልል ተወካዮች በምክር ቤቱ ውስጥ አለመሳተፋቸው እንደ ዋና ምክንያት ይጠቀሳል።

የብሪጅ ዳሰሳ እንደሚያሳየው፣ በሥድስቱ የምርጫ ዘመናት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውስጥ የወንዶች ድርሻ 81 በመቶ ሲሆን፣ የሴቶች ደግሞ 19 በመቶ ብቻ ነው። ይኽ አማካይ ውጤት እንደሚያሳየው በፌዴሬሽን ምክር ቤት ያለው የሴቶች ውክልና ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አንጻር ሲታይ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ነው። ምንም እንኳ በተለያዩ የምርጫ ዘመናት የቁጥር መዋዠቅ ቢታይም፣ ባለፉት ሥድስት የምርጫ ዘመናት በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሴቶች ውክልና አማካይ ዕድገት 3.88 በመቶ ብቻ ሆኖ ተመዝግቧል። ይኽ የውክልና ማነስ በምክር ቤቱ የሕገ-መንግሥት አጣሪ ጉባኤ ውስጥም ይስተዋላል። የሕገ-መንግሥት አጣሪ ጉባኤ በአገሪቱ የሕግ የበላይነት እና የሕገ-መንግሥት ትርጓሜ ላይ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ተቋም ቢሆንም፣ የሴቶች ተሳትፎ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙባቸው ተቋማት መካከል ተጠቃሽ ሆኗል። ይኽም በከፍተኛ የሕግ ትርጓሜ እና የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የሴቶች ድምፅ እና አመለካከት አኹንም በተገቢው ኹኔታ እንዳልተካተተ ማሳያ አድርገን ልንቆጥረው ይቻለናል።

## የሴቶች ውክልና በእንደራሴዎች ምክር ቤት

| ተ.ቁ. | የምርጫ ዘመን | የሴት አባላት ቁጥር | የሴቶች ድርሻ (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|
| 1 | 1ኛው (1987 – 1992) | 14 | 2.6 በመቶ |
| 2 | 2ኛው (1993 – 1997) | 42 | 7.7 በመቶ |
| 3 | 3ኛው (1998 – 2002) | 117 | 21.4 በመቶ |
| 4 | 4ኛው (2003 – 2007) | 152 | 27.8 በመቶ |
| 5 | 5ኛው (2008 – 2013) | 213 | 38.9 በመቶ |
| 6 | 6ኛው (2014 – 2019) | 197* | 41.7 በመቶ |

**በ6ኛው የምርጫ ዘመን አልያም አኹን በሥራ ላይ ባለው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ውስጥ የሴቶች ምጣኔ ከቀደመው ዝቅ ብሎ የሚታየው፣ በወቅቱ በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት ምርጫ ባልተካሄደባቸው አካባቢዎች የተነሳ ክፍት የሆኑ ወንበሮች በመኖራቸው እንጂ በመቶኛ ሲሰላ ግን 41.7 በመቶ በመድረስ በታሪክ ከፍተኛው መሆኑን ልብ ይሏል።*

## የሴቶቹ ተሳትፎ በቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ

| ተ.ቁ. | የአገልግሎት ዘመን | የቋሚ ኮሚቴዎች ብዛት | የሴት ሰብሳቢዎች ቁጥር (በመቶኛ) | የሴት ምክትል ሰብሳቢዎች ቁጥር (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 1988 – 1992 | 9 | 1 (11 በመቶ) | 1 (11 በመቶ) |
| 2 | 1993 – 1997 | 12 | 1 (8 በመቶ) | 1 (8 በመቶ) |
| 3 | 1998 – 2002 | 13 | 3 (23 በመቶ) | 4 (31 በመቶ) |
| 4 | 2003 – 2007 | 16 | 4 (25 በመቶ) | 5 (31 በመቶ) |
| 5 | 2008 – 2009 | 18 | 7 (39 በመቶ) | 10 (56 በመቶ) |
| 6 | 2010 – 2011 | 20 | 8 (40 በመቶ) | 10 (50 በመቶ) |
| 7 | 2011 – 2013 | 10 | 6 (60 በመቶ) | 2 (20 በመቶ) |
| 8 | 2014 | 11 | 5 (45 በመቶ) | 4 (36 በመቶ) |
| **አማካይ** | 1988 – 2014 | - | 31.5 በመቶ | **30** በመቶ |

***ጨመቃዊ ነጥቦች፤***

* *ሴቶች በቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢነት ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ከ2011-2013 ዓ.ም*
* *. ሲሆን፣ ይኸም 60 በመቶ (ከ10 ኮሚቴዎች 6ቱን በመሰብሰብ) ነበር።*
* *ምክትል ሰብሳቢነት፦ ከ2008-2009 ዓ.ም. የነበረው የሴት ምክትል ሰብሳቢዎች ቁጥር 56 በመቶ በመድረስ ከወንዶቹ በልጦ የታየበት ብቸኛው ወቅት ነበር።*
* *አጠቃላይ አማካይ፤ ባለፉት 26 ዓመታት ውስጥ የሴቶች የአመራር ተሳትፎ በአማካይ 31 በመቶ ገደማ ደርሷል።*

## የሴቶች ውክልና በፌዴሬሽን ምክር ቤት

| ተ.ቁ. | የምርጫ ዘመን | ጠቅላላ ወንበር | የሴት አባላት ቁጥር | የሴቶች ድርሻ (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 1ኛው (1987 – 1992) | 110 | 7 | 6.7 በመቶ |
| 2 | 2ኛው (1993 – 1997) | 112 | 8 | 7.1 በመቶ |
| 3 | 3ኛው (1998 – 2002) | 120 | 22 | 18.3 በመቶ |
| 4 | 4ኛው (2003 – 2007) | 135 | 24 | 17.7 በመቶ |
| 5 | 5ኛው (2008 – 2013) | 153 | 50 | 32.6 በመቶ |
| 6 | 6ኛው (2014 – 2019) | 144 | 43 | 30 በመቶ |
| **ጠቅላላ** | 1987 – 2019 | 774 | 154 | 19 በመቶ (አማካይ) |

***ጨመቃዊ ነጥቦች፤***

* *በፌዴሬሽን ምክር ቤት ታሪክ ከፍተኛው የሴቶች ተሳትፎ የታየው በ5ኛው የምርጫ ዘመን ሲሆን፣ በወቅቱም 32.6 በመቶ ደርሶ ነበር።*
* *ባለፉት ሥድስት የምርጫ ዘመናት የሴቶች አማካይ ውክልና 19 በመቶ አካባቢ ሲሆን፣ ይኽም ከእንደርሴዎቹ ምክር ቤት አንጻር ሲታይ መጠነኛ ዝቅታ ያሳያል።*

***ከላይ ያሉት ሦሥቱም የአሃዛዊ መረጃዎ ዘንጠረዦች የተሰናሰሉት በእንደራሴ መጽሔት ነው።***

## የብሪጅ ምክረ-ሐሳቦች

ከላይ በደምሳሳው እንዳየነው፣ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎም ሆነ፣ በተያያዥ መለከያ የሚሆነው የእንደራሴነት ጾታዊ ምጣኔ፣ ሰፊ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶችም፣ መፍትሔዎችም ቢኖሩትም ቅሉ፣በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ሊተገበሩ የሚችሉ ሕግ እና ፖሊሲ ነክ ምክረ-ሐሳቦች ላይ ብቻ መታጠርን መርጠናል። ከዚኽ አንጻርም፣ ተከታዮቹን አጭር ፖሊሲ ነክ ምክረ-ሐሳቦችን ማጋራት እንሻለን።

* **አስገዳጅ የጾታ ኮታ ሥርዓትን በሕግ መደንገግ፤**

በኢሕአዴግ ዘመነ-መንግስት የሴቶች ውክልና በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ቢጨምርም፣ ይኽ ዕድገት በሕግ የተደገፈ ሳይሆን በፓርቲው የውስጥ ያልተጻፈ መመሪያ ላይ የተመሰረተ ነበር። በብልጽግና ፓርቲ ዘመነ-መንግስትም ከፍተኛ የመንግሥት የሥልጣን እርከኖች ለሴቶች ቢሰጡም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ደረጃ ውክልናን የሚያረጋግጥ አስገዳጅ የሕግ ማዕቀፍ ገና አልተዘረጋም። እንደ ብሪጅ ዕምነትም፣ የሴቶች ውክልና በፓርቲዎች በጎ ፈቃድ ወይም ባልተጻፈ መመሪያ ላይ ብቻ እንዲመሰረት መተው የለበትም። ከዚኽ አንጻርም፣ የሴቶች ውክልና በገዥው ፓርቲ ጊዜያዊ በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ እንዳይወድቅ፣ በምርጫ ሕጉ ውስጥ ለሴት ተወዳዳሪዎች የተወሰነ ዝቅተኛ የኮታ መጠን (ለምሳሌ 30 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ) በግልጽ ተደንግጎ እንዲቀመጥ ማድረግ ያስፈልጋል ብለን እናምናለን።

* **የቋሚ ኮሚቴ አመራርነትን በጾታ ስብጥር ማመጣጠን፤**

የብሪጅ ዳሰሳ እንደሚያሳየው ሴቶች በገቢ፣ በሰላም፣ በውጭ ጉዳይ፣ በበጀት እና በኢኮኖሚ ነክ ቋሚ ኮሚቴዎች ላይ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው። ስለዚህም፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤቱ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችን እና ምክትል ሰብሳቢዎችን ሲመድብ፣ ሴቶች በኹሉም (በተለይም በኢኮኖሚ እና በደኅንነት) ኮሚቴዎች ውስጥ የላቀ የአመራር ድርሻ እንዲኖራቸው የሚያስገድድ የውስጥ የምክር ቤቱ መመሪያ መቀረጽ ይኖርበታል ብላ ብሪጅ ታምናለች።

* **የፓርቲ ውስጥ ዴሞክራሲን ከማዕከላዊ ቁጥጥር ወደ አካታችነት ማሻገር፤**

በኢሕአዴግ ዘመን የእጩዎች ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በተሰኘው የግንባሩ መርህ የሚመራ በመሆኑ፣ ሴቶች ለዕጩነት የሚቀርቡት ከላይ በሚመጣ ቀጥተኛ ውሳኔ እንጂ በታችኛው መዋቅር ፍላጎት አልነበረም። ብዙዉን የፓርቲ መዋቅር ከኢሕአዴግ መውረሱ ብዙም በማያከራክረው ብልጽግናም ይኽ ከፍተኛ የአመራር ተዋረድ ቁጥጥር እንደቀጠለበት ይስተዋላል። እናም፣ ፓርቲዎች በውስጥ አሠራራቸው ግልጽ፣ ተወዳዳሪ እና ከማዕከላዊ ተፅዕኖ ነፃ የሆነ የእጩ ምልመላ ሥርዓት ቢዘረጉ ፋይዳው ብዙ መሆኑን ከላይ በዳሰሳዊ ነጥቦች ከማየታችን አኳያ፣ ብሎም በምክር ቤቱ አብላጫ ወንበሮችን የያዘው ብልጽግና ፓርቲ ነውና፣ ድርጅቱ ይኽን ምክረ-ሐሳብ ቢያጤነው ሴቶች በራሳቸው ብቃት እና በሕዝብ ድጋፍ እንዲወጡ

ዕድል የሚሰጥበትን ሰፊ አገራዊ ኹኔታ ያመቻቻል ማለትን እንሻለን።

* **ለሴት ዕጩዎች የፋይናንስ እና የቁሳቁስ ድጋፍ ማመቻቸት፤**

የኢትዮጵያ የትኞቹም ምርጫዎች እና ለመሳተፍ የሚካሄዱት የምርጫ ዘመቻዎች በርከት ያለ የፋይናንስ እና የቁሳቁስ ድጋፍ ግድ የሚሉ መሆናቸው ይታወቃል። ይኽም ለሴቶች ተሳትፎ ትልቅ እንቅፋት መሆኑን ብዙ ጥናቶች ይጠቁማሉ። እንደ ብሪጅ ዕምነትም፣ መንግሥት እና የምርጫ ቦርድ ለሴት ዕጩዎች የሚሰጡትን መንግሥታዊ ድጋፍ ከወንዶች በተሻለ መልኩ የሚጨምርበትን አሠራር ቢዘረጉ ፋይዳው ብዙ ይሆናል። በዚኽ መሰሎቹ ድጋፎች መኖርም፣ ቢያንስ ሴቶቹ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ከምርጫ ፉክክሮች እንዳይገለሉ ይሄ ነው የሚባል አበርክቶ ይኖረዋልና። ከዚኽ ባለፈም፣ ለሴት ዕጩ እንደራሴዎች ብቻ የሚውል የተለየ የመንግሥት የምርጫ ፈንድ ማቋቋም እና የግል ለጋሾች ለሴት ዕጩዎች ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ የሕግ ማዕቀፍ ማበጀትም ቢታሰብበት እንላለን።

* **የምርጫ ሥርዓት ቅየራ፤**

ምንም እንኳን ቀጣዩ 7ኛ ብሔራዊ ምርጫ፣ በሕገ-መንግሥቱ በተቀመጠው መሠረት፣ አሸናፊው ፓርቲ መንግሥት የሚመሠርትበት 'ፈርስት-ፓስት-ዘ-ፖስት' የተሰኘው፣ አሸናፊው ኹሉን የሚወስድበት ጠቅላይ-የበላይ ሊሰኝ የሚችል የምርጫ ሥርዓትን ተከትሎ እንደሚተገብር ብናምንም፣ ቢያንስ ይኽኛው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የምርጫ ሥርዓቱ ቢያንስ በቀጣዩ ምርጫ ይቀየር ዘንድ ግፊት ሊያደርግ የሚችልበትን አማራጭ ማስሰ እንደሚኖርበት ማስታወስ እንሻለን። የዚኽ የምርጫ ሥርዓት መኖር፣ ሴቶቹ ወደ እንደራሴነት እንዳይመጡ ካገዷቸው መዋቅራዊ መሰናክሎች አንዱ መሆኑን ያስታውሷልና። የምርጫ ሥርዓቱን ወደ ተመጣጣኝ ውክልና አልያም ኹለቱን ወዳደባለቀ ሥርዓት መቀየር፣ ለሴቶች የተሻለ የውክልና ምጣኔ መንገድ መጥረጉንም ብሪጅ ማስታወስ ትሻለች።

* **ዜግነታዊ ደኅንነትን ማስጠበቅ፤**

በቀደሙት ጊዜያቶች የነበረው ጾታ-ተኮር ጫና ብዙም በአደባባይ ያልወጣ እና መዋቅራዊ ነበር። በአኹኑ ዘመን እንደምንመለከተው ግን፣ ሴት ፖለቲከኞች በማኅበራዊ ሚዲያ እና በአካል ግልጽ የሆኑ ስድቦች፣ ማስፈራሪያዎች እና ጾታ-ተኮር ጥቃቶች ሰለባ ሲሆኑ ይታያል። በሴት ፖለቲከኞች እና የአደባባይ የመብት አራማጆች ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን፣ የቃላት ስድቦችን እና ማስፈራሪያዎችን የሚከላከል እና ወንጀለኞችንም ተጠያቂ የሚያደርግ ጠንካራ የሕግ ከለላ ማበጀት። ለቀጣዩ ትውልድ ጭምር ፋይዳው ብዙ ነውና ቢታሰብበት ስትል ብሪጅ ማስታወስ ትሻለች።

* **የሕግ አውጪውን የሥራ አካባቢ ለሴቶች ምቹ ማድረግ፤**

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመሰብሰቢያም ሆነ የሌሎች የምክር ቤቱን ሥራዎች የተመለከቱ የሥራ ሰዓቶችን፣ የሕፃናት ማቆያ አገልግሎትን እና የጾታዊ ጥቃት መከላከያ

ደንቦችን በማሻሻል ለሴት እንደራሴዎቹ ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠር እንዳለበት አሌ አይባልም። እናም፣ እንደ እንደራሴ መረዳት፣ ምክር ቤቱ ይኽን ማድረጉ ሴቶች የቤተሰብ እና የፖለቲካ ሕይወታቸውን በአግባቡ እንዲመሩ እና በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በሚኖሩ ውይይቶች እና ወሳኝ ስብሰባዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ያበረታታልና፣ ቢታሰብበት ማለት እንወዳለን።

* **የመረጃ አያያዝ እና የጾታ ትንታኔ ማዕቀፍን ማጎልበት፤**

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሚያወጣቸው ሕግጋት እና በሚያጸድቃቸው በጀቶች በሴቶች ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ለመገምገም የሚያስችል ጾታ-ተኮር ትንታኔ የሚከውንበት አሠራር ሊኖረው እንደሚገባው ግልጽ ነው። ከዚኽ ባለፈም፣ በየደረጃው ያለውን የሴቶችን ውክልና የሚመዘግብ እና ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆን ወቅታዊ የመረጃ ማቆሪያ ሥርዓት በምክር ቤቱ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በኩል ቢጠናከር፣ ተቋማዊ ጥቅሙ ብዙ መሆኑን ብሪጅ ታምናለች፤ እናም፣ ይኽንን ምክረ-ሐሳብም የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ቢያጤነው ማለትን እንሻለን።

## ፍካሬ ዘ እንደራሴ

“እንደራሴ” የሚለው ንባበ-ቃል በኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ የፖለቲካ ተዋስዖ እና የሥነ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ግዝፈት የነሳ ፍካሬያዊ ንባበ-ቃል ነው። የቃሉ ከየት መጥነት እና ፍካሬም፣ በአጠቃሎ መልኩ ይኽን መሰል ፍቺዎች ነበሩት/አሉትም።

ንባበ-ቃሉ የተገኘው “እንደ” እና “ራሴ” ከሚሉ የኹለት ቃላት ጥምረት ነው። “እንደ”፦ መስያ፣ ፈንታን ወይም ምትክን ሲያመለክት፤ “ራሴ”፦ ራስ ጠሪውን ማንነት አልያም ባለቤቱን-ሲፈከርም ባለሥልጣኑን ያነጽራል። በአማሪያዊ ፍቺውም፣ “እንደ እኔ” ወይም “እኔን ሆኖ” ማለት ነው ይቧል። በኢትዮጵያ ሥነ-መንግሥት ታሪክ “እንደራሴ” የሚለው ማዕረግነቱን ሲያጣቅስ፣ በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነበረው፤ ለማሳያ፦

ሀ- የንጉሠ ነገሥቱ ተወካይ (በፈረንጅ አፍ- Regent እንዲሉ)፦ በንጉሣዊው ሥርዓት ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ በአንዳች ምክንያት (ለዐቅመ-መንበር ባለመድረስ፣ በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት) አገረ-መንግሥቱን መምራት ካልቻሉ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶት አገሪቱን የሚያሥተዳድረው ሰው “ቢትወደድ-እንደራሴ” ይባል ነበር።

ለ- የአካባቢ ወይም የክፍለ-ሀገር ገዢነት፦ ንጉሠ ነገሥቱ በየክፍለ ሀገራቱ ‘ራሳቸው ዘወትር መገኘት ስለማይችሉ፣ በ‘ርሳቸው ስም የሚፈርዱ እና የሚያሥተዳድሩ ተወካዮቻቸውን “እንደራሴ” ይቧቸዋል፤ ይኽም የንጉሡ ምሉዕ ተወካይነትን ይሰጣል።

ሐ-የሕዝብ እንደራሴነት፦የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ከመጣ ወዲኽ ግን ቃሉ አዲስ ፍካሬ ያዘ። ሕዝቡ በ‘ራሱ ፈንታ ሆኖ በምክር ቤት እንዲመክርለት እና ውሳኔም እንዲሰጥለት የሚመርጣቸው ሰዎች “የሕዝብ እንደራሴዎች” መባል ጀመሩ። የዚኽ ፍካሬም፣ “ሕዝቡን ሆኖ የሚሠራ”፣ “ምስለ-ሕዝብ” አልያም “የሕዝቡ ተወካይ” የሚል ትርጓሜን አሰጠው።

ዛሬ “ተወካይ” (በምዕራቡ የምክር ቤት ታሪክ ጅማሮ-Representative-እንዲሉ) ከሚለው ቃል ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ ያገለግላል። ሆኖም “እንደራሴ” የሚለው ቃል ከውክልና ባለፈ፣ የወከለውን አካል ሙሉ ክብር እና ማንነታዊ ተዛምዶ ይዞ የሚገኝ ክብደት ያለው ፖለቲካዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ፍካሬ አለው።

## የብሪጅ አፈካከር

ተቋማችን ብሪጅ፣ የአማርኛን ሰዋስው ደንብ ጠብቃ፣ ይኽንን ቃል ከኋለኛው ወደዚኽ ዘመን አናጥቃ በመፈከር ተጠቅማለች። አስቀድመን ሊቃውንቱ ያስቀመጡትን እንጥቀስ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፣ እንደ ራሴ፣ እኔን ሆኖ፣ የእኔን ሥልጣን ይዞ የሚሠራ ብለው ሲፈቱት፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በፈንታ፣ በምትክ የሚቆም ሲሉት፤ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጸው በተራቸው፣ ተለዋጭ፣ ተወካይ፣ ባለሙሉ ሥልጣን የሚል ፍቺ ይሰጡታል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልም ቢሆኑ፣ አንድ ሰው በራሱ ስም ሳይሆን በሌላው ስም ተገኝቶ የሕግ ተግባራትን ሲያከናውን እንደራሴ መባሉን ያነሳሉ። እነዚኽ ዋቢዎች እንደሚያሳዩት፣ ቃሉ በመጀመሪያ ለነገሥታት ተወካዮች ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ ኋላ ለሕዝብ ተወካዮች እንዲሠራበት የተደረገው የሕዝቡን ልዕልና ለመግለጽ ውለዋል፤ አለፍ ሲልም፣ ተወካዩ ሕዝቡን ሆኖ ይገኛል፤ እንደ ሕዝቡ ሆኖ ይጠራል የሚለውን ፍካሬ ይሰጣሉ።

በዚኽ አግባብ፣ “እንደራሴ” ስንል፦ አንድም ራስ የሚለውን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ከቆመበት ‘የራስን ዕድል በራስ የመወሰን’ ሕገ-መንግሥታዊ ነባር መርህ ጋር አናጽረን ፈክረነዋል። ይኽ ማለት፣ በዚኽ መርህ ውስጥ ያለው ‘ራስ’፣ የሚለው ትርጉም የሚጠቅልላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በ “እንደራሴ” ውስጥ ያለውን ‘ራሴ’ን ለመፍታት ፍካሬያዊ ትርጓሜን ተጠቅመናል። ከዚያ ባለፈም፣ በቀደመው ዘመን መራጩ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነው ሁሉ፣ በዚኽኛው የእኛው ዘመን ሕዝብ ነውና፣ “እንደራሴ” ስንል፦ እንደ መረጠው ሕዝብ፣ ብሔረሰብ አልያም ብሔር የሆነ በሚል ፍቺ መጠቀማችንን ልብ ይሏል። በዘመናዊው የምርጫ ሥርዓት ስናነጽረውም፣ መራጩ ግለሰብ እንደራሴውን ‘ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በመንበሬ’ ሲል፣ በነገረ-ሕይወቱ ይወስንለት ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ መርጦ ይልከዋል። የመረጠውም እንደራሱ ካልሆነለት፣ ምስለ እኔነቱን ሊነጥቀው መቻሉን ያስረግጣል።

የ“እንደራሴ” ንባበ-ቃል፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ሲቋቋም፣ የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ በዘመኑ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው አማርኛ ብቻ ቢሆንም ቅሉ፣ ንባበ-ቃሉ ግን በሌሎቹ የአገራችን የብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎች ውስጥም መገኘቱን ልብ ይሏል፤ ለማሳያ፦ በሲዳማ- amaalete mina፣ በአፋን ኦሮሞ-Bakka bu’aa፣ በትግሪኛ- ከማይ፣ በወላይተኛ Kal Ati-ya/Taga ton መባሉን ያስታውሷል።

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

አንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።


BRIDGE Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 99 808 5013

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, O ce No. 5, Addis Ababa.